# በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከቃል ኪዳን፣ ከፈውስ፣ ከስያሜ እና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች ጥናት

ዮሴፍ ቦኪ*


### *Abstract*

*The main purpose of this article is to analyze the narratives in connection with covenant, healing, naming and the hagiography of Abune Tekle Hayemanot himself. The data were basically collected through in-depth interview and observation. The data were analyzed using hermeneutically interpretation and inter-textual analysis based on theories of functionalism and narratology. The study has identified that a number of patients were healed through various spiritual practices: such as drinking holy water and nifro wuha[1], lapping one's body with the cross, steaming with a smoke of the kitchen of Debre Libanos and caring the book of hagiography of Abune Teklehaymanot. The paper has shown that numerous healings were done which might not be justified by the worldly reality. Naming in this study was given due attention for its denotative and connotative interpretation. The origins and symbolic representations of some basic names were narrated and analyzed. To this end, the narratives in relation to the covenant, healing, naming and the hagiography of St. Teklehaymanot were identified as a significant instrument to teaching, maintaining and transferring the religious ideology and spiritual identity of the monastery to the next generation.*


*Key words: Narrative, Covenant, Cure, Name and Abune Tekle Haymanot*

*ዲያቆን ዮሴፍ ቦኪ መዳ ወላቡ ዩኒቨርስቲ የሥነ ጽሑፍ እና የሕዝብ ጥበብ (Foklore) መምህር ናቸው።

[1]Nifro wuha is a kind of water left after cooking as waste product.

# ፩. መግቢያ

## ፩.፩ የጥናቱ ዳራ

ደብረ ሊባኖስ ገዳም የምሥረታው ታሪክ ከአቡነ ሊባኖስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጋር እንደሚያያዝ ይነገራል። አቡነ ሊባኖስ ለብዙ ዘመናት በሥፍራው ተወስነዋል (በተጋድሎ)። ኋላም ሌላ ታላቅ ሐዋርያ እንደሚነሣና ክብሩ በእርሱ እንደሚበለጽግ ተነገራቸው። በመታሰቢያነት ሥፍራው ለዘለዐለም በስማቸው እንደሚጠራም እንዲኹ። በዚኽም ቦታው ለ፺፱ ዐመታት ጠፍ ኾኖ እንደ ቆየና ኋላ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደ ቀና ይገለጻል።[2]

አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተወለዱት በ፲፩፻፺፯ ዐ.ም. በቡልጋ እቲሳ ጽላልሽ በተባለ ሥፍራ ነው። አባታቸው ጸጋ ዘአብ ከአቡነ ቄርሎስ (ጌርሎስ)[3] ዘንድ ወስደው ዲቁና፣ ኋላም ቅስና አሰጣቸው።[4] በቆይታም እናትና አባታቸው ሞቱ። በቤተሰብእ ዕቅፍ የመኖራቸው ቀዳሚ ምዕራፍ እዚኽ ላይ ይቋጫል ("ቋ" ይጠብቃል)፤ በዚያው ቅጽበት በእግዚአብሔር ረድኤት የተጋድሎ ፈር ይበጅላቸዋል (ለምሳሌ፡ የስም ለውጥ፣ ስዕመት ...)። ወዲያው ተጋድሎዋቸውን ከበቀሉበት ሥፍራ (ቡልጋ) ይጀምራሉ። ከጥንቱ የዳሞት ግዛት አኹን ወላይታ ተብሎ እስከሚጠራው ዞን ለ፲፪ ዐመታት አስተምረዋል።[5] ከድንበር አስማሪዎች ጋርም በመንፈስ ጸጋ እየተፋለሙ፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተዘዋውረዋል (ለምሳሌ፤ በሐይቅ፣ በትግራይ፣ በደብረ ዳሞ...)፤ ፈርጀ ብዙ ተጋድሎዎችንም ፈጽመዋል።[6]

የጻድቁን ሕይወትና የገዳሙን አመሠራረረት በክለሣ ድርሳናት ላይም ስለምንመለስበት ስለ ተረክ ጥቂት እንበል። የአንድን ማኅበረሰብ የሕይወት ፍልስፍና፣ የእምነት ሥርዐት፣ ከፈጣሪው ጋር ያለውን ትባሬ ወይም ተራክቦ፣ ከየት መጣነት እንዲሁም ሥነ

---

[2]አባ ኃይለ ሚካኤል ወልደ አምላክና ሌሎች (በዚህ መልክ ስገለገል መረጃ ያቀበሉኝ አባቶች ሁሉ በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ ሐሳብ እንዳላቸው ለማጠየቅ ነው።)፣ ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት ፳፻፺ ዐ.ም.። ዳንኤል ክብረት፣ የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፣ ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፣ ፲፱፻፺፱ ዐ.ም.፣ ገጽ ፬፻፳፰፤ ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ ዐማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፹፪ ዐ.ም.፣ ገጽ ፪፻፵፪።

[3]መረጃ ያቀበሉኝ አባቶች እንዲኹም በ፲፱፻፹፱ ዐ.ም. የታተመው *ገድለ ተክለ ሃይማኖት (ገ.ተ.ሃ.)* ጭምር "አቡነ ጌርሎስ" ነው የሚሉት (መምህር ኃይለ ሚካኤል ወልደ አምላክና ሌሎች፣ ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት ፳፻፺ ዐ.ም.፤ ገ.ተ.ሃ፤፲፱፻፹፱፣ ገጽ ፳፫÷፲፱)። በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው አቡነ ጌርሎስ (ቄርሎስ) የሚሉም አሉ (ዳንኤል፣፲፱፻፺፱ ዐ.ም.፣ ገጽ ፵፤ ተክለ ጻድቅ፣ ፲፱፻፶፩ ዐ.ም.፣ ገጽ ፲፪-፲፬)።

[4] ሥርግው፣ ፲፱፻፹፪ ዐ.ም.፣ ገጽ ፪፻፵፪፤ Taddesse Tamrat, Church and State in Ethiopia: 1270-1527, London, Oxford University press, 1972, p. 36.

[5]ዳንኤል ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፴፩።

[6]ሥርግው፣ ፲፱፻፹፪፡፪፻፵፪፤ Taddesse, 1972: 161-163.

ልቡናዊ ማንነት ለመረዳት ተረኮች ሚናቸው ትልቅ ነው፡፡ ተረኮች የአንድን ማኅበረሰብ የማንነት አሻራ ያንጻሉ፤ ብሎም ይገነባሉ፡፡ በገዳማት የሚገኙ ተረኮችን ማጥናት ደግሞ ገዳሙንና የገዳማውያኑን ርእዮት ለመረዳት ያስችላሉ፡፡ ስለኾነም በገዳሙ የሚነገሩ ተረኮችን (**ቃል ኪዳን፣ ፈውስ፣ ስያሜ እና አቡነ ተክለ ሃይማኖትን** የሚያጠይቁ (ጥናቱ የተመሠረተባቸውን)) ሳይንሳዊ በኾነ ብሂል የማጥናቱ ምክንያትም ከዚኹ የመነጨ ነው፡፡ በርግጥ ገዳሙ በነገረ መለኮትና በታሪክ የሙያ መስኮች ተፈትሿል፤ ተመርምሯል፡፡ ዳሩ ግን ንጽረታቸው አንድም ከነገረ ሃይማኖት፤ አንድም ከታሪክ አይወጣም፡፡

## ፩.፪ የጥናቱ ዐላማዎች

### ፩.፪.፩ ዋና ዐላማ

በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም **ከ*ቃል* *ኪዳን*፣** **ከ*ፈውስ*፣** **ከ*ስያሜ*** እና *ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር* በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮችን መፈከር፤ እንዲኹም ፋይዳቸውን መተንተን ነው፡፡

### ፩.፪.፪ ዝርዝር ዐላማዎች

በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከ**ቃል** *ኪዳን ጋር* በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮችን ከሚያነሷቸው ጽንሰ ሐሳቦችና ድርሳናት ጋር እያዛመዱ መመርመር፣

- በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም *ከፈውስ ጋር* የሚገናኙ ተረኮችን መተንተን፣
- በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም *ከስያሜ ጋር* ተዛማጅ የኾኑ ተረኮችን እና የተረኮቹን ፋይዳ መተንተን
- በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከራሳቸው *ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት* ማንነት ጋር የተያያዙ ተረኮችን መፈከር ናቸው፡፡

## ፩.፫ ክለሣ ድርሳናት

### ፩.፫.፩ የደብረ ሊባኖስ ገዳም የስያሜ ታሪክ አመጣጥ

በአቡነ ሊባኖስ አመጣጥ ዙሪያ በጽሑፍ የሚገኙም ኾነ በቃል የሚነገሩ የተለያዩ ዘመናትን የመጠቆም ጠባይ ይታይባቸዋል፡፡ ተስዓቱ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳን) ከመምጣታቸው በፊት መጡ የሚሉ፤ በኋላ ነው የሚሉም አሉ፡፡ ዳንኤል[7] ትንሣኤ መጽሔትን ጠቅሶ በአምስተኛው መ.ክ.ዘ. የነበሩ ጻድቅና ተስዓቱ ቅዱሳን በመጡ በሰባተኛው ዐመት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ይጠቁማል፡፡ በቅድሚያ በኤርትራ ቀጥሎም በአኵስም ተቀምጠዋል፡፡ የአኵስሙን ንጉሥ በመገሠጻቸው ተበሳጭቶ ያሳድዳቸዋል፡፡በመጨረሻም ወደ ሸዋ

[7] ዳንኤል፣ ፲፱፻፺፱ ዐ.ም፡፡

ተጉዘው በዜጋ መል (ደብረ ዐስቦ) ተቀምጠዋል፡፡ ኋላም ሥፍራው በኋለኛው ዘመን ለሚነሣው ጻድቅ የተዘጋጀ ነውና ክፍልህ ወደ ኾነው ትግራይ ሒድ፤ ሥፍራው ለዘላለም በስምህ ይጠራል እንደተባሉና ወደ ትግራይ እንዳቀኑም ያብራራል፡፡[8] በሌላ ሥፍራ ደግሞ ስለ ደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሠራረት ሲገልጽ በአራተኛው መ.ክ.ዘ. በአቡነ ሊባኖስ እንደ ተቋቋመ ተጠቅሷል፡፡[9] ሌሎች ምሁራንም ስለ አቡነ ሊባኖስ ጽፈዋል፤ አቡነ ሊባኖስ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በአራተኛው መ.ክ.ዘ. እንደ ኾነ፡፡[10] በአንድ በኩል ጊዜው በውል ሳይጠቀስ ከተስዓቱ ቅዱሳን መምጣት በፊት አቡነ ሊባኖስ ኢትዮጵያ እንደገቡ የሚያትቱም አልጠፉም፡፡፡[11] ልዩነቱ መረጃ ባቀበሉኝ አባቶች ዘንድም ጭምር ነው፡፡ አባ ኪዳነ ማርያም እና አባ ኃይለ ሥላሴ ከአቡነ ሊባኖስ መምጣት ጋር በተያያዘ ዘመኑን ፮፻፲፰ ዐ.ም. (ሰባተኛው መ.ክ.ዘ.) በማድረግ ይጋራሉ፡፡[12] አባ ወልደ ገብርኤል ምሕረቱ ደግሞ ወደ ፭፻፵ ዐ.ም. ያመጡታል፡፡[13] በመጨረሻም ገዳሙ ባዘጋጀው ምስል ወድምፅ ዘጋቢ ፊልም ውስጥ የሚጠቀሰው ደግሞ አራተኛው መ.ክ.ዘ. ነው፡፡ ተስዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ በገቡ (፬፻፹ ዐ.ም አካባቢ) በሰባተኛው ዐመት የሚለው የሚያስማማና የሚያቀራርብ ይመስለኛል፡፡ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት አስተያየቶች የተለየ ሐሳብ የሚያቀርቡም አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ሊቀ ኅሩያን በላይ መኰንን አንዱ ናቸው፡፡

አባ ሊባኖስ (መጣዕ) ከተስዓቱ ቅዱሳን ቀደም ብለው ወይም በነሱ ዘመን እንደ መጡ ማጠየቂያው ቅዱስ ያሬድ (፭፻፭-፭፻፸፩ ዐ.ም.) በድጓው ከዘመረላቸው ቅዱሳን አንዱ መኾናቸው ነው፡፡[14] በገዳመ አስቄጥስ-ግብጽ ከ፭ኛው አባት ከአባ ጳኵሚስ ሥርዐተ ምንኵስናን እንደ ተቀበሉ በስንክሳሩ ስለ ተገለጸ ቀዳሚነታቸውን ያስረዳል፡፡

አባ ሊባኖስ (መጣዕ) የመሠረቱት ገዳም በአካለ ጉዛይ አውራጃ-ኤርትራ የሽመዛናውን ደብረ ሊባኖስ እንደኾነ በታሪክ ይታወቃል፡፡

> The Monastery of Debre Libanose … is located in the historical district of Anbeset Geleba, Shimezana, in the present day southern part of the province of Akkale Guzay, Eritrea close to the border with Agame, Tigray. የደብረ ሊባኖስ ገዳም መገኛ ቦታ በታሪካዊው አንበሰት ገለባ - ሽመዛና ወረዳ፣ በዛሬው ደቡባዊ የአካለ ጉዛይ አውራጃ፣ ኤርትራ፣ ከአጋሜ- ትግራይ አዋሳኝ ቦታ ላይ ነው፡፡[15]

[8]ዳንኤል፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፵፫፡፡

[9]ዳንኤል፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፬፻፳፰፡፡

[10]መንግሥቱና አሳምነው፣ ፳፻፣ ገጽ ፳፡፡

[11]ብርሃኑ ገብረ አማኑኤልና ሌሎች፣ ፲፱፻፺፣ ገጽ ፳፫፤ ሥርግው, ፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፻፲፰፡፡

[12]ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቊጥር 3A-B እና 4A-B, መጋቢት ፳፻፲ ዐ.ም፡፡

[13]ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቊጥር 2A-B, መጋቢት ፳፻፲ ዐ.ም.፡፡

[14]መጽሐፈ ድጓ ጥር ፭፡፡

[15]Alesandro Bausi. Encyclopaedia Aethiopica. Vol. II, 2005, pp. 28-29. Taddesse Tamerat

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የአዳሉን እስላማዊ ገዢ በድላይን ለመውጋት ወደ ጦርነት ሲሔድ የደብረ ዐስቦ ገዳም መነኰሳት በጸሎት እንዲያስቡት አደራ ሰጥቶ ሒዶ ነበር፡፡ በድል አድራጊነት ሲመለስም በገዳሙ አበ ምኔት አባ እንድርያስ አማካይነት መነኮሳቱ አቀባበል ሲያደርጉለት የገዳሙን መጠሪያ ‹‹ደብረ ሊባኖስ›› ብሎ ሰየመው፡፡[16]

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በሕፃንነት ዕድሜው እናቱ ለአባ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን አደራ ሰጥታው በአካባቢው ስላደገ ‹‹ደብረ ሊባኖስ›› የሚለው ስም ለእሱ ዐዲስ አይደለም፡፡ በዚያ ዘመን የሽመዛናው ደብረ ሊባኖስ ገዳም በጣም የታወቀ ነበር፡፡ እናም ይኽንን ስም ለደብረ ዐስቦ ገዳም ሰጠ፡፡ ተጉለት አካባቢ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያን በግብጽ ሀገር በምትታወቀዋ ቤተ ክርስቲያን ስም ‹‹ደብረ ምጥማቅ›› ብሎ እንደ ሰየመ ኹሉ፡፡ ወይም ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ፩ኛ ጎንደር ላይ በቅድስት ሥላሴ ስም የመሠረተውን ቤተ ክርስቲያን የሸዋውን ‹‹ደብረ ብርሃን ሥላሴ›› ስም ወስዶ እንደ ሰየመው ማለት ነው፡፡

## ፩.፫.፪ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ልደትና ዕረፍታቸው

በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ልደትና ዕረፍት ላይ የተለያዩ ዘመናት ተጠቅሰዋል፡፡ ያነጋገርኳቸው አባቶች በሙሉ የትውልድ ዘመናቸውን ፲፩፻፺፯ ዐ.ም. ዕረፍታቸውን ደግሞ ፲፪፻፺፰ ዐ.ም. ያደርጉታል፡፡ በአጠቃላይ የኖሩበት ዘመንም ፺፱ ዐመታት ከ፲ ወራት ከ፲ ቀናት ይኾናል ማለት ነው፡፡ ዳንኤል የልደታቸውን ዘመን ፲፩፻፹፮ ዐ.ም ነው ይላል፡፡[17] ምሁራን በጉዳዩ ላይ የሰነዘሩትንም ይጠቅሳል፡፡ ዐፄ ይኵኖ አምላክ (፲፩፻፷፫-፲፪፻፸፰ ዐ.ም.) ሥልጣን ሲይዝ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፹ ዐመታቸው ነበር። ይኽም የልደት ዘመናቸውን ፲፩፻፺ ዐ.ም. ያደርገዋል፡፡ ጌታቸው ኃይሌ ደግሞ ፲፪፻ ዐ.ም. ነው ይላሉ፡፡[18] ዳንኤል በ፲፪፻፹፯ ዐ.ም. በ፺፱ ዐመታቸው እንዳረፉ ሲገልጽ፣ ተክለ ጻድቅ ደግሞ በ፲፪፻፷፮ ዐ.ም. በ፻፩ ዐመታቸው ማረፋቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ኹለቱም ላይ ክፍተት ይስተዋላል፡፡ የዳንኤልን ስንመለከት፣ ከ፲፩፻፹፮ -፲፪፻፹፯ ዐ.ም. የኖሩበት ዘመን እንደ ኾነ ጠቁሟል፡፡ ሲሰላ ፻፩ ዓመት ይመጣል። ስለዚኽ ቀድሞ ከሰነዘረው ጋር የ፪ ዐመታት ልዩነት አለው።የተክለ ጻድቅ ደግሞ ከ፲፩፻፶፪-፲፪፻፷፮ ዐ.ም. ነው፡፡ እርሳቸው በአጠቃላይ የኖሩበትን ዕድሜ ፻፲ በማለት አስረድተዋል፡፡ የጠቀሱት ዘመን ሲለካ ደግሞ ፻፲፬ ዐመት ይመጣል፡፡ ይኽም በመኃል የ፬ ዐመት ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡[19] ሥርግው የኖሩበት ዘመን ከ፲፪፻፫-፲፫፻፬ እንደ ኾነ ያወሳሉ፡፡[20] በሌላ ሥፍራ ደግሞ የልደት ዘመናቸውን ፲፪፻፬

1972, p. 24.

[16]ዳንኤል ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፬፻፴፡፡

[17]ዳንኤል፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፴፪፡፡

[18]ጌታቸው፣ ፳፻፮፣ ገጽ ፪፻፴፬፡፡

[19]ዳንኤል፣ ፲፱፻፺፱፡፴፪፣ ገጽ ፵፬፤ ተክለ ጻድቅ፣ ፲፱፻፶፩፣ ገጽ ፲፯-፲፱፡፡

[20] ሥርግው፣ ፲፱፻፹፪፣ ገጽ ፻፵፪፡፡

ያደርጉታል።[21] ታደሠ ታምራት ከ፲፪፻፲፫-፲፫፻፲፫ ኢ.ኤ.አ እንደኖሩ ይገልጻል።[22] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ክፍል የሚዘጋጀው ትንሣኤ መጽሔት ውስጥ የተጠቀሰው ዘመን ከላይ መረጃ አቀባዮቼ ከነገሩኝ ጋር ይገጥማል።[23] እኔም ይኽን ሐሳብ እጋራለሁ።

### ፩.፫.፫ የተረክ ብያኔ በተለያዩ ምሁራን ዕይታ

በሕዝባዊ ጥበብ (ፎክሎር) ቤት ከሚጠኑ፣ ከሚመረመሩና ከሚተነተኑ አያሌ ጉዳዮች መካከል ተረክ አንዱን ሥፍራ ይይዛል። ተረክ ከ፲፰ኛው መ.ክ.ዘ. አንሥቶ ራሱን የቻለ ሙያ ኾኖ ሲቀነቀን የኖረ መስክ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በልዩ ልዩ እሳቤዎች እየተቃኘ እና በርእዮተ ዐለም እየተገራ፣ በተለያዩ ሙያዎች (ለምሳሌ፤ በሥነ ሰብእ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በሥነ መለኮት፣ በታሪክ፣ ወዘተ…) ውስጥም ዘልቆ ቤተኛ እየኾነ መጥቷል። የተረክ ጥናት በአስገራሚ አእምሮአዊ ንቃትና ብቃት የበለጸገ መኾኑን ዶርሰን[24] ያስረዳል። በአንድ በኩል ነገረ ተረክ (Narratology) እየተባለ የተረክ ንድፈ ሐሳብ ኾኖ ግዳጁን ይፈጽማል። በዚኹ ጠገግ ንድፈ ሐሳቡ (Narratology) በተረኮች ውስጥ ያሉ ታሪኮችን፣ ምስሎችን፣ ድርጊቶችን እንዲሁም ኹነቶችን ለመረዳት፣ መተርጐም እና ለመተንተን እንደሚበጅ ልሒቃኑ ይዘክራሉ።[25]

ተረክ "Narrative" የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ይተካል።[26] ቃሉ እንደየ ሀገሩና እንደየ ልሒቃኑ የተለያዩ ስያሜዎች አሉት። እነዚኽ ስያሜዎች ዐለም ዐቀፋዊ ያይደሉ፤ ይልቁንም አካባቢያዊ እንደ ኾኑ በልሒቃኑ ጽሑፍ ውስጥ ሲጠቀስ ይስተዋላል። ባስኮም በየ ሀገሩ ያሉ ስያሜዎችንም በከፊል ለመግለጽ ሞክሯል።[27] ጀርመኖች ተረክን "Marchen" ብለው ሲጠሩት አሜሪካኖች ደግሞ የጀርመኖችን ወደ እንግሊዝኛ መልሰው "Folktale" እንደሚሉት ያስረዳሉ።። ጀርመኖችም ኾኑ አሜሪካኖች "Marchen" እና "Folktale" ሲሉ ሦስቱንም የቃላዊ ዝርው ተረክ ዐይነቶችን (ተረት፣ ሚት እና አፈ ታሪክ) ባካተተ መልኩ መኾኑንም ይገልጻሉ። ይኹን እንጂ ዝርው ተረክ ጀርመኖችም አሜሪካኖችም ከሚሉት የተለየ እና የጽሑፋቸው ዐላማም ልዩነቱን እማሳየቱ ላይ <u>እንደሚያዘነብል</u> ያትታል። ፈቃደ በበኩሉ "ተረት" ይለዋል።[28]

[21] ሥርግው፣ ፲፱፻፸፩፣ ገጽ ፻፳።
[22] ታደሠ ታምራት ፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፴፯። በጥናት የተሠራ ስለ ኾነ ታደሰ፣፲፱፻፸፪ የተሻለ ነው።
[23] ትንሣኤ መጽሔት፣ ፲፱፻፸፫፣ ገጽ ፲፳።
[24] ዶርሰን፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፸፫፣ ገጽ ፻፷።
[25] Bal, 1997, p. 5; Brockmeier and Carbaugh, 1984, p. 4.
[26] እንዲኽ ማለቴ ዶ/ር ዮናስ አድማሱን መነሻ በማድረግ ነው። ዶ/ር ዮናስ አድማሱ "አስረኛንኩዋ። ሐዲስ ዐለማየሁና የማኅበራዊ ሒስ ስልታቸው" በሚለው መጣጥፋቸው ውስጥ "*Narrative*" የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል "ተረክ" በሚለው መልሰውና አቻ አድርገው ተገልግለውበታል። እኔም ይኽን ሐሳብ ስለምጋራ የእርሳቸውን አሰረ ፍኖት ተከትዬ ዘልቄያለሁ ፲፱፻፺፪፡ ገጽ ፹፬።
[27] Bascom,1965, pp. 3-4.
[28] ፈቃደ፣ ፲፱፻፺፩ ዐ.ም.፣ ገጽ ፶፪።

 © ጥናትና ምርምር ማእከል ፣ ማኅበረ ቅዱሳን

በሌላ በኩል ኦሪንግ[29] “Narrative” የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል Relate ካለው የላቲን ቃል የተተረጐመ እንደ ኾነ እና በታሪክ ነገራ ላይ ተመሥርቶ የሰዎችን ትውስታ እና የቃላት አጠቃቀም የመፈተን ኀይል ያለው እንደ ኾነ ያስረዳል:: በጥቅሉ ጀርመኖች፣ አሜሪካኖች እንዲሁም ፈቃደ (፲፱፻፺፩) እንደሚለው “ተረክ”ን ያህል ፅንሰ ሐሳብ አንድ አካሉ በኾነው በ“ተረት” ቅጥር ውስጥ ማኖሩ በ“ግብታዊ” ፍርድ ስሕተት ይመስለኛል:: ተረክ ቀዳሚ ማኅደሩን ንዶ (ጀርመኖች፣ አሜሪካኖች እና ፈቃደም[30] ጭምር እጅጉን አጥብበው/ወስነው ያሰመሩትን ድንበር) በተለያዩ እሳቤዎች እየ ታሸ፣ በርእዮተ ዐለም እየ ተቃኘ እጅጉን በሚያስደንቅ ፍጥነት እየ ቀና ያለ ተለጣጭ ሐቲት (flexible discourse) ነው። ባስከምም[31] ብሂሎቻቸውን (የጀርመኖችንና የአሜሪካኖችን) ተችቷል::

ተረክ አንድም በዝርው፤ አንድም በግጥማዊ ቅጥ ይቀርባል:: የተረክ ዐይነቶች ከሚባሉት ውስጥ ሚት፣ አፈ ታሪክ፣ ተረት፣ የእንስሳት ተረቶች፣ ዐጫጭር ታሪኮች፣ ኤፒክ፣ ታሪክ፣ አሳዛኝ ታሪክ፣ ድራማ፣ ተውኔት፣ አዝናኝ ታሪክ፣ ሥዕል፣ ፊልም፣ የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው::[32] ባስኮም[33] የሚጎራበቱትን እያዋገነ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከቅርጽ አንጻር በሦስት መድበዋቸዋል፤ ሚት፣ አፈ ታሪክ እና ተረት በማለት:: ሚትንና አፈ ታሪክን[34] ማእከል ያደረጉ ተረኮች (በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ከኹለቱ ጉዳዮች የሚወጡ አይመስለኝም (ወዲኽ ሚታዊ ናቸው፤ ወዲያ ደግሞ አፈ ታሪካዊ ወጎች) የዚኽን ጥናት ጉዞ የሚያቀኑ ማሔጃዎች ናቸው::

## ፩.፬ የጥናቱ ዘዴ

ወዲኽ መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰንደዋል፤ ወዲያም የተሰነዱት ተረኮች በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ እና በተረክ ንድፈ ሐሳብ መታገጊያነት ተፈክረዋል፤ ተተንትነዋል:: ተረኮቹን በይነ-ጽሑፎች[35] (inter-textual) ማድረጉም ሌላኛው ብልሃት ነው:: በሕዝብ ጥበብዊ ጉዳዮች ዘርፍ ምርምሩን ለማድረግ የሚነሣ ተመራማሪ ምልከታና

---

[29]ኦሪንግ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፹፮፣ ገጽ ፻፳፫::

[30]ፈቃደ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፶፪::

[31] ባስኮም፣ ፲፱፻፷፭፣ ገጽ ፫-፬::

[32]ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፪፻፶፱-፪፻፷፤ Finnegan, 1992:36; Franzosi, 1998:517; Oring, 1986, p. 123

[33] ባስኮም፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷፭፣ ገጽ ፭::.

[34]ሚትና አፈ ታሪክ አንድም ኹለትም ናቸው:: ተፋቅሮም ተቃርኖም ይስተዋልባቸዋል። ኹለቱም ቃላዊ ዝርው ተረኮች መኾናቸው እና ክሡት በሚኾኑበት ማኅበረሰብ ውስጥ እውነትነትን መጎናጸፋቸው በትይዩ እንዲቆሙ ያደርጋቸዋል:: በገጸ ባሕርያት አሳሳል (አንዳንዴ የአፈ ታሪክ ገጸ ባሕርያት ከልዕለ ተፈጥሮ ወገን የሚቆጠሩበት አጋጣሚ አይጠፋም)፣ ድርጊትና ኹነትን አጣምሮ በያዘው የመቼት አቀራረብ እና በመንፈሳዊነት ወይም በቅድስና (አንዳንዴ በአፈ ታሪክ ውስጥ ከሥጋዊ ጉዳይ ባሻገር መንፈሳዊ ወይም የተቀደሰ ሐሳብ የሚነሣበት አጋጣሚም አለ) ረገድ ልዩነት ይንጸባረቅባቸዋል::

[35]Krishnaswamy, 2004, p. 154; wolfreys, Julian and Others, 2006, p. 58. የሕዝብ ጥበብ ጥናት ሥፍራ ባገኘበት በዚኽ ወቅት፣ “በይነ ጽሑፋዊ” የመፈከሪያ ብልሃት ጽሑፎችን እያቃየጠ ፍቺ መፈልቀቂያ ኾኗል። “በይነ ጽሑፋዊ” በሥነ ጽሑፍ ቤት ሚናው እልፍ ነው:: ከሚናው አንዳች ሳናጎድል ከነሙሉ ክብሩ በሕዝብ ጥበብ ቤትም አዝልቀን እንገለገልበት ዘንድ ይቻለናል:: “በይነ ጽሑፋዊ” በጽሑፎች መካከል የሐሳብ መፈላለግና የፍቺ መቃለጥ የሚፈከርበት ነው:: ጽንሰ ሐሳቡ የሚዳኘው ጽሑፍ ከሌሎች ጽሑፎች ያስተጋባቸው ሐስቦች መኖራቸውን የምንመረምርበት ብሎም ፍቺ የምናለምድበት ሥልትና ማኼጃም ጭምር ነው::

ቃለ መጠይቅን ቢገለገል ተመራጭ እንደ ኾነ ያስረዳል፡፡[36] ምልከታን አጥኚው በወጉ የያዘውና የተገለገለበት እንደ ኾነ በተሻለ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ዘዴው ከአፍኣዊው ዕይታ በተጨማሪ ውሳጣዊ ወይም ልቡናዊ ሕዋሶችን የሚያተጋ በመኾኑ ስለ ጥቅል የክንውኑ ሒደት ምልዓት ያለው መረጃ ሊያስገኝ ይችላል፡፡[37]

ቃለ መጠይቅ ከሚታወቅ መረጃ አቀባይ ጋር በጥያቄና መልስ የሚከወን ሒደት ነው፡፡ ምልከታና ቃለ መጠይቅን ቀይጦ የመገልገሉ ሥልት፣ በትባሬያቸው ትግግዝ ወግ ያለው መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ በመኾናቸው ነው፡፡ እዚኽ ላይ መረጃ ሰብሳቢው ኹለቱን ዘዴዎች አዋግኖ የማቅናቱ ብልሃት እግምት ውስጥ ይገባል፡፡[38] በአጠቃላይ በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚስተዋሉ ሃይማኖታዊ ተግባራትን፣ የገዳማውያኑን ድርጊት እና በተረኮቹ የሚዘከሩ ሥፍራዎችን ለመቃኘት ምልከታን ተገልግያለሁ፡፡ ቃለ መጠይቅ ደግሞ በገዳሙ ከቃል ኪዳን፣ ከፈውስ፣ ከስያሜ እና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮችን ለመሰብሰብ አገልግሏል፡፡

በተመረጡት ተረኮች ላይ ፍካሬ ለማሔድና አንድምታዊ ፍቺዎችን ለመፈልቀቅ ቀደም ብዬ የገለጽኳቸው ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functionalism Theory) እና የተረክ ንድፈ ሐሳብ (Narrative Theory /Narrotology) እጅጉን ተስማሚ ኾነው ተገኝተዋል፡፡

# ፪. የተረኮቹ ትንተና

## ፪.፩ ከቃል ኪዳን ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

ቃል ኪዳን ኹለትና ከዛ በላይ በኾኑ ሰዎች መካከል ነገሩን ለማጽናት የሚደረግ መሐላ ነው፡፡[39] በየትኛውም ኪዳናዊ ብሂል ውስጥ ቃል ኪዳን ሰጪ፣ ተቀባይ እና ተስፋ ይገኛሉ፡፡
በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከሚነገሩ ተረኮች መካከል በዚኹ ጠገግ የቀኑና ኪዳናዊ ሐሳብ የነገሠባቸው ተረኮች ይገኛሉ፡፡ ተጋዳልያን በአንድ ዘመን ለተለየ ዐላማ ክሡት የሚኾኑ ናቸው፡፡፡ ዐላማቸውም ማኅበረሰባቸውን ከመከራ፣ ከጭንቅ፣

---

[36]Goldstein, 1964, p. 77.

[37]Goldstein, 1964, p. 63; ፈቃደ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፺፫፡፡

[38]Goldstein, 1964, pp.77-78.

[39]የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ፲፱፻፺፪፣ ገጽ ፺፪፤ ፩ኛ ሳሙ ፲፰÷፫-፬፡፡ ቃል ኪዳኑ አንድም በተራ ሰው እና በፈጣሪ፤ አንድም በተከበረ ሰው እና በፈጣሪ መካከል ሊካሔድ ይችላል፡፡

ከጠላት፣ ወዘተ... መታደግ ወይም ነጻ ማውጣት ወይም ለማኅበረሰባቸው ጽድቅና ረድኤት ማስገኘት ሊኾን ይችላል[40]።

እኒኽ ተጋዳልያን ወደ ተሰማሩበት ቀጠና ዘምተው ግዳጃቸውን ፈጽመው ሲመለሱ ለአካባቢያቸው ብሎም ለሀገራቸው የሚያስገኙት አንዳች በረከት ይኖራል። ይኽን ቃል ኪዳን ብለን ማሰብ የምንችል ይመስለኛል። ምክንያቱም በአንድ በኩል በተጋድሎ ብዛት የሚገኝ ፍሬ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ለተፈጸመው ተጋድሎ በብድራትነት የሚከፈል ዋጋ ነውና። ነገሬን በተረኩ ላጽና፤

> የመሞቻቸው ቀነ ቀጠሮ ሲደርስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱን ድንግል ማርያምን፣ ዮሴፍና ሰሎሜን፣ እልፍ አእላፍ መላእክትን፣ ነቢያትና ሐዋርያትን፣ ጻድቃንና ሰማዕታትን አስከትሎ መጣ። "በደጅህ መጥቶ የተማጸነውን በገነት አኖርልሃለሁ፤ በመንግሥተ ሰማያት ፲፰ አህጉራት ላንተ ይኹኑ፤ ዘርህን ፲ ትውልድ ድረስ እምርልሃለሁ፤" ብሏቸው አርጓል።[41]

በተረኩ የተለያዩ ጉዳዮች ተነሥተዋል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም እስከ ሰማዕታት ድረስ በማዕረግ አስከትሎ መምጣት አንዱ ነው። ይኽ የክብር ተዋረድን ያሳያል። የክርስትና እምነት መሠረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኾነ። በመኾኑም "ራስ"[42] ወይም "በኵር"[43] የሚል ስያሜ ይሰጠዋል።

---

[40]የትኞቹም ተጋዳልያን ወገኖቻቸው በተጨነቁ፣ መከራ በተጫናቸው፣ ታላቅ ቀውስ በነገሠበት ወቅት የሚደርሱ መልእክተኞች ወይም የሚወለዱ አዳኞች ናቸው። ዳሩ ግን፣ ዐለም በ"እንኳን ደህና መጣህ" ልቡን ከፍቶ፣ ፊቱን ፈትቶ፣ እጁን ዘርግቶ አይቀበላቸውም። የማኅበረ አቋሙ ጠባቂዎች - ክፉ ንጉሥ፣ ቀናተኛ አባት፣ ተንኮለኛ ዘመድ፣ ወዘተ. ለሞት ያጯቸዋል። ሀገረ ገዥው ካምሣ ዘመዱን ጌታ ክሪሽናን ሊገድለው አሳድዶታል። ንጉሥ ሄሮድስ ጌታ ኢየሱስን ፈልጎ ባጣ ጊዜ በቤተልሔም የአይሁድ ሕፃናትን በሰይፍ አስፈጅቷል። ንጉሥ ሌዉስ ልጁን፣ ኤዲፐስን ለአውሬ አስጥሏል። ፈርዖን የእስራኤል ወንድ ሕፃናት ታንቀው እንዲገደሉ፣ ውኃ ውስጥ እንዲጣሉ አዟል፣ ወዘተ...(ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፵፬)።

[41]አባ ኃይለ ሥላሴ ወልደ አማኑኤል፣ ካሴት ቁጥር 4A-B, መጋቢት ፳፻፫ ዓ.ም.።

[42]ነገር ግን በፍቅር እውነተኞች እንኾን ዘንድ ራስ ወደ ኾነው ወደ እርሱ ወደ ክርስቶስ እንደግ (ኤፌ ፬÷፲፭)። በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኊልና የሕንፃው የማዕዘን ራስ ድንጋይም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ኤፌ ፭÷፳)። እርሱ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። በኵር እርሱ ለኹሉ ራስ ይኾን ዘንድ ከሙታን ኹሉ አስቀድሞ ተነሥቷልና (ቆላ ፩÷፲፰)።

[43]"በኵር" የግእዝ ቃል ሲኾን በዕብራይስጥ ቤኩራቲ እንደሚባልና ትርጕሙም የመጀመሪያ ልጅ ማለት እንደኾነ ይገልጻል። አባ ጀሮምን ጠቅሶ ብቸኛ ልጅ ኹሉ የበኵር ልጅ ነው። የበኵር ልጅ ኹሉ ግን ብቸኛ ልጅ አይደለም ይላል። ኢየሱስ ክርስቶስ በኵር የተባለበትን ምክንያት ቅዱስ አትናቴዎስን ዋቢ አድርገው ይኽን ብለዋል፤ "ኢየሱስ ክርስቶስ በኵር የተባለው ከእኛ አስቀድሞ ስለ ሞተ አይደለም። ነገር ግን ስለ እኛ ሞቶ ሞትን ድል በመንሣቱ ነው። ትንሣኤን በእርሱ ከእርሱ በኋላ ስለምናገኘው ነው" (ዐባይነህ፣ ፳፻፪፣ ገጽ ፻፳፫-፻፳፰)። ድኅነትን ያገኘንበት፣ ኀጢኣታችን የተሰረየበት ነው። ይኸውም የማይታይ እግዚአብሔርን የሚመስለው፣ ከፍጥረቱ ኹሉ በላይ የኾነ በኵር ነው (ቆላ ፩÷፲፭-፲፰)።

ከዚኽ በመነሣት "የቤተ ክርስቲያኒቱ በኵር ከተከታዮቹ ጋር ወደዚኽ ሥፍራ መጣ" ተብሎ መተረኩ አንድም የገዳሙን፤ አንድም የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቅድስና ለመዘከር ተገልግለውበታል ማለት ይቻላል፡፡

ሌላው "በደጅህ መጥቶ የተማጸነውን በገነት አኖርልሃለሁ" የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለሃያ ዘጠኝ ዐመታት ያህል በገዳሙ፣ ከዚያም በፊት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለፈጸሙት ተጋድሎ የተገባላቸው ኪዳን እንደኾነ እንረዳለን፡፡ በእግዚአብሔር ታጭተው መላ ዕጣ ፈንታቸው በመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ላይ የወደቀ[44]፣ ለአንዳች መንፈሳዊ ግዳጅ የተለዩ ተጋዳሊ ናቸው፡፡ ስለዚኽ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት የተገባላቸው ቃል ኪዳን አንድም የወገኖቻቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ክፍተት የሚሞላ፤ አንድም መንፈሳዊ ንጥፈትና ድቀታቸውን የሚጠግን፤ አንድም መንፈሳዊና ቁሳዊ የበረከት ምንጭ ሊኾን ይችላል፡፡ "በመንግሥተ ሰማያት ዐሥራ አምስት አህጉራት ላንተ ይኹኑ፤ ዘርኽን እስከ ዐሥር ትውልድ ድረስ እምርልሃለሁ" መባሉም ለዚኹ ሳይኾን አይቀርም፡፡

ከቃል ኪዳን ጋር በተያያዘ ሐሳቡን የሚያበለጽግ ሌላ ተረክ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ወዳጄ ተክለ ሃይማኖት ልጆችህ እንደ ባሕር አሸዋ፣ እንደ ሰማይ ከዋክብት ይበዛሉ፤ እንኳንስ በሕይወተ ሥጋ ልጆችህ ያንተን ስም እየጠሩ እኔን የሚለምኑት ይቅርና የጸለይክባት፣ ያለቀስክባት ይኽቺ ምድር ጦም አታድርም ብሎ ቃል ኪዳን ገባላቸው፡፡[45]

በተረኩ ከሚተኮርባቸው ጉዳዮች መካከል "እንደ ባሕር አሸዋ፣ እንደ ሰማይ ከዋክብት ይበዛሉ" ቀዳሚው ነው፡፡ በሚት ልማድ ውስጥ ገናን ከኾኑት ጉዳዮች መካከል የተቃራኒዎች ግጥምጥም የሚጠቀስ ሲኾን ዋነኛ የተረኩ ማዝለቂያ ኾኖም ግዳጁን ይፈጽማል፡፡ የ"ባሕር አሸዋ" እና የ"ሰማይ ከዋክብት" በኹለንተናቸው ተቃርኖ (ተቃራኒ) እንጂ ተፋቅሮ (ኅባሬ) የላቸውም፡፡ አሸዋ ምድራዊ፣ ከዋክብት ደግሞ ሰማያዊ፡፡ አንድም አሸዋ ለሰው ልጅ የኢ-ንቁ አእምሮ፣ ከዋክብት ደግሞ ለንቁ አእምሮ ውክሎች ይመስሉኛል፡፡

ቀደም ብዬ አሸዋ ምድራዊ፣ ከዋክብት ደግሞ ሰማያዊ ብያለሁ፡፡ በዚኽ ተርታ እንየውና በአንድ በኩል አሸዋ ለምድራውያን፣ ከዋክብት ደግሞ ለሰማያውያን ትእምርቶች ናቸው፡፡ ምን ማለቴ ነው፤ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ኃጥኣንም ጻድቃንም ይገኛሉ፡፡ ኹለቱም በአንድ ዐውድ ውስጥ ሰፍረው በዐላማም፣ በሙያም ይቃረናሉ (በአንድ የአእምሮ ቅጥር ውስጥ የሚያድሩት ንቁና ኢ-ንቁ የአእምሮ ክፍላትም ብሂላቸው ከተግባራቸው፣ ሙያቸው ከግባቸው ፈጽሞ አይገጥምም)፡፡ ኃጥኣኑ ምድራዊ ለኾነው ጉዳይ አብዝተው የሚጨነቁ

[44]ገድለ ተከክለ ሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱፡፳፯÷፴፫-፵፤ ፵፯÷፰፤ ፲÷፴፫-፴፯፤ ፴፯÷፲፩፤ ፴፰÷፻፹- ፻፴፬።
[45]አባ ወልደ ገብርኤል ምሕረቱ፣ ካሴት ቍጥር 2A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም.፡፡

(በተጋድሎ ያልጸኑ፣ በእኩይ ግብር የተነደፉና እሱኑ የሚያቀነቅኑ)፣ ይልቁንም ለእንግዳው ዐለም እስብ ሥፍራ የነፈጉ፤ ጻድቃኑ ደግሞ ምድራዊ ኾነው ንጽረታቸው ሰማያዊ የኾነ፣ ለእንግዳው ዐለም ሥፍራ የቸሩ፣ በተጋድሎ የጸኑ ልንላቸው እንችላለን። ስለኾነም አሸዋ ለኃጥኣን ወይም ለምድራዊው እስብ፣ ከዋክብት ደግሞ ለጻድቃን ወይም ለሰማያዊው እስብ የቆሙ ትእምርቶች ናቸው ማለት ይቻላል። በዚኽም ገዳም የጻድቅ መገኛ ብቻ ሳይኾን የኃጥኡም ማደሪያ ነው። የጻድቁ ጽድቅ በኃጥኡ ይገለጣል፤ አንዱ የአንዱን መኖር ይሻል፤ መኖሩንም ያውጃል፤ ብርሃንም በጨለማ ሀልዎቱ ይጸናል። የተቃራኒዎች የመቃየጥና የመቃለጥ ወጉ ይኽም አይደል?

ቀጥሎ ደግሞ፣ "እንኳን በሕይወተ ሥጋ ልጆችህ ያንተን ስም እየጠሩ እኔን የሚለምኑት ይቅርና የጸለይክባት፣ ያለቀስክባት፣ ይኽቺ ምድር ጦም አታድርም" የሚለው ዐረፍተ ነገር ሲኾን እርሱን ወደ ማየቱ እንመለስ።

በደብረ ሊባኖስ በቀን ቢያንስ አንድ ሰው ሳይቀበር ውሎ እንደማያውቅ ይነገራል። ከተለያየ ቦታ መጥቶ የሚቀበር ሰው ቢጠፋ እንኳ ከገዳሙ ማኅበረሰብ አንዱ ሞቶ መቀበሩ አይቀርም (በመስክ ቆይታ ያስተዋልኩት ጉዳይ ነው)። የዚኽ ምክንያቱ ደግሞ "ምድሪቱ ጦም አታድርም" ከሚለው ኪዳን የመነጨ መኾኑ ተተርኳል። ጉዳዩ የሰውና የመሬትን ተራክቦ የሚያጸና ይመስለኛል። ሰው መሬት (አፈር) እንደ ነበርና ከመሬት እንደ ተሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።[46] ዞሮ መግቢያውም እንዲኹ፤ "አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና።[47]

ፋሽስት ኢጣሊያ በሀገራችን ጦርነት በከፈተበት ወቅት አቡነ ጴጥሮስ "እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምድሪቱም አትገዛልህ" ማለታቸውን ታሪክ ይዘክራል።[48] ይኽ ሐሳብ ከላይ ላነሣሁት ጉዳይ ወግኖ ነገሬን የሚያበለጽግ ነው። የሰው ልጅ ፍልስፍናውን በተለያዩ ቅጦች ያስቀምጣል። ከፍልስፍና ማኖሪያ መንገዶቹም አንዱ ቃላዊ ተረክ ነው። ስለኾነም በተረኩ ውስጥ ሰውና መሬት ተቃይጠው፣ አንዱ ለሌላው መነሻና መዳረሻ ኾኖ የሚኖር፣ በዚኽም አንድ የኾኑ ኹለቱ ጉዳዮች አብረው ኪዳን ሲቀበሉ እንመለከታለን።

ተረክ ሰማንያ ዘጠኝ[49] ሌላው ኪዳናዊ ሐሳብ የተነገረበት ነው። በተረኩ ጌታ ኢየሱስ

[46]ዘፍ. ፪÷፯።

[47]ዘፍ. ፫÷ ፲፱።

[48]መንግሥቱና አሳምነው፣ ፳፻፣ ገጽ ፪፻፴፰።

[49]እንዲኽ ያሉ አኃዛዊ መግለጫዎች በጥናቱ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ይገጥሙናል። በጥናቱ ሒደት ከገዳሙ (ደብረ ሊባኖስ) ዘጠና ስምንት ያህል ተረኮችን ለመሰብሰብ ተችሏል። ተረኮቹም በይዘታቸው በተለያዩ ዐሥራ አንድ መደቦች ተከልለዋል። ለዚኽ ጥናትም አራቱ መደቦች፣ (ቃል ኪዳን፣ ፈውስ፣ ስያሜ እና አቡነ ተክለ ሃይማኖት) ብቻ ተመርጠዋል።

ክርስቶስ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃል ኪዳን ሲገባላቸው፣ "ቦታህ እኔ እንደ ተወለድኩባት ቤተልሔም፣ እንደ ተጠመቅኩባት ዮርዳኖስ፣ እንደ ተሰቀልኩባት ቀራንዮ፣ መቃብርህም እኔ እንደ ተቀበርኩባት ጎልጎታ፣ ሥፍራህም ለኢትዮጵያውያን የመማጸኛ ከተማ ይኹንልህ" ብሏቸዋል፡፡[50]

ደብረ ሊባኖስ ገዳም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌ ከተመላለሰባቸውና ተአምራትን ከፈጸመባቸው ከቤተልሔም፣ ከዮርዳኖስ፣ ከቀራንዮ እና ከጎልጎታ ጋር የማዋገኑ ልማድ በተረኩ ቀርቧል፡፡ ወዲኽ ታሪካዊ ወዲያም የሃይማኖታዊ ክዋኔዎች ማረፊያ የኾኑ ሥፍራዎች በማንጸሪያነት ይቆማሉ፡፡ ይኽ አንድም በቤተ እምነቱ የሚገኙ ጽንሰ ሐሳባዊና ርእዮተ ዐለማዊ ተራክቦዎችን ያጸናል፤ አንድም ኹነቱ ለገዳማውያኑም ለአማንያኑም አእምሯዊ እና ልቡናዊ ጽናትን ብሎም ርካታን ይተክላል፤ አንድም በታሪካዊና በሃይማኖታዊ ሥፍራዎቹ ማሔጃነት የገዳሙን ህልውናና ከፍታ የማላቅ ሚናን የተሸከመም (ተረኩን ማለቴ ነው) ይመስላል፡፡

## ፪.፪ ከፈውስ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

በደብረ ሊባኖስ ገዳም የጎበጡ ቀንተዋል፤ በአጋንንት እስራት የተያዙ ተፈትተዋል፤ ከእከክ ስቃይ ድነዋል፤ አውሬ ከሆዳቸው ወጥቷል፤ ከአስም ተፈውሰዋል፤ ዐይናቸውን ያጡ በርተዋል፤ ዐይተውማል፤ መስማት የተሣናቸው ሰምተዋል፡፡ እኒኽን የፈውስ ዐይነቶች በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ቀዳሚው ከአካላዊ ሕመም መዳን ነው፡፡ የዐይን መብራት፣ የጆሮ መስማት፣ የስብራት መጠገን፣ የጎበጠ መቅናት፣ ወዘተ ...፡፡ ሌላኛው ፈውስ፣ ከአጋንንት እስራት ነጻ መውጣት ነው፡፡ በዚኽ ውስጥ የሚከናወነው ውጊያ ከረቂቃን መናፍስት ጋር ነው፡፡ የመጨረሻው ፈውስ ከሙታን ተለይቶ መነሣት ነው፡፡[51]

በተረኮቹ የተከናወነው የፈውስ ሒደት በጠበል፣ በተግባር ቤት (ዳቤ፣ ጭስ፣ ንፍሮ ውኃ) እና በመስቀል አማካይነት ነው፡፡ ተረክ ስልሳ አራትና ስልሳ ስድስት በአንድ መንፈስ የተቃኙ በመኾናቸው አዋግኜ እመለከታቸዋለሁ፡፡ በተረክ ስልሳ አራት አንድ አእምሮው የታመመ፣ ራሱን መቆጣጠር የማይችል ሰው እንደነበር፣ ኋላም ተግባር ቤት ወስደውት እዚያም በጭስ፣ በዳቤና በንፍሮ በኹለንተናው ድኅነት እንዳገኘ ተነግሯል፡፡[52]

በተመሳሳይ በተረክ ስልሳ ስድስትም አንድ ከጎጃም የመጡ ዐይነ ሥዉር እንደ ነበሩና ተግባር ቤት ገብተው ዳቤ እየበሉ፣ የንፍሮ ውሃ እየጠጡና በጭስ እየታጠኑ የማያይ ዐይናቸው እንደበራ ተተርኳል፡፡[53]

[50] ጸባቴ አባ ወልደ ማርያም አድማሱ፣ ካሴት ቁጥር 7A, መጋቢት ፳፻፯ ዓ.ም፡፡

[51] ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፻፲፫-፻፲፮፡፡

[52] አባ ኃይለ ሥላሴ ወልደ አማኑኤል፣ ካሴት ቁጥር 4A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

[53] አባ ሠረገላ ገብረ ሕይወት፣ ካሴት ቁጥር 5A, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

በኹለቱም ተረኮች የፈውሱ ክዋኔ የተፈጸመው በተግባር ቤት ነው:: እዚኽ ላይ የልዩ ልዩ ነገረ ድኅነት ጣጣ እንቆቅልሽ በኾነበት ዓለም፣ ይኾናል ተብሎ የማይታሰብ፣ ጭራሽ የማይገመት ይልቁንም ጤናን ያውካል፣ ዐይን ያሳውራል በሚባለው ጭስ እንዲሁም በዳቤ፣ በንፍሮና በንፍሮ ውሃ ፈውስ እንደተከናወነ መነገሩ በገዳሙ የሚፈጸመው ፈውስ አንድም ከዐለማዊው ጥበብ በተቃርኖ የቆመ፤ ኹለንተናዊውንና ነባራዊውን ሐቅ ለመገዳደሩ በማሳያነት የተተረከ ሊኾን ይችላል (እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያን ወይም ገዳማት ዐለማዊውን የሕክምና ጥበብ ይቃወማሉ ማለቴ እንዳይደለ ይታወቅ)፡፡

ወዲህ ልቡናዊና አእምሯዊ ዝንጋኤ፣ ወዲያ ደግሞ በሰበበ ፈውስ አስተርእዮ-ርእስ (self-discovery)[54] ክሡት የኾነ ይመስለኛል፡፡ ምን ማለቴ ነው፤ በነገረ ፈውስ ማሔጃነት (“ፈውሱን” ምክንያት ልንለው እንችላለን) ራሳቸውን ገልጠዋል (በድኅነት ተቃኝተዋል)፤ ራሳቸውን ዐውቀዋል፤ የጠፋ ማንነታቸውን አግኝተዋል፡፡ ሲዘልቅ ከተነጠሉት ማኅበረ ባህላዊ ውቅር ጋር ኑባሬን ይነድፋሉ፤ ወግ ባለው ሥርዐትና ልማድ ለመኖርም ፈር ያበጃሉ፡፡ በአፍኣም በውስጥም (በልቡና) የጠፋ ማንነታቸውን አግኝተዋልና፡፡

> በጠበል የተፈጸመ ወይም የተከናወነ ሌላ የፈውስ ሒደት አለ፡፡
> አንድ ወገቡ የጎበጠ፣ አቀርቅሮ የሚሔድ ተማሪ ነበር፡፡ በትምህርት ቤት ለብዙ ዐመታት ሲንገላታ ኖሯል፡፡ በእግዚአብሔር ፍቃድ፣ በጻድቁ ምልጃ በጠበል ተፈውሶ ቀና ብሎ መሔድ ቻለ፡፡[55]

ጠበል ሕመምተኞች ፈውስ ለማግኘት የሚጠጡት ወይም የሚጠመቁበት፣ የተጸለየበት ወይም በፈጣሪ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተባረከ ውኃ ነው፡፡[56] በተጨማሪ በተአምራት የፈለቀ ከደዌ የሚያድን፣ የሚፈውስ ነው፡፡[57] ጠበል ድኅነትን ወይም ፈውስን ወክሎ የቆመ ትእምርት ይመስለኛል። ምክንያቱም ጠበል ሲባል ነገረ ድኅነት ተከትሎ የሚመጣ ጉዳይ ነውና (በተለይ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች)፡፡ በሐዲስ ኪዳን ጠበል[58]

---

[54]ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፺፡፡ አስተርእዮ ርእስ (self-discovery) አንደኛ፣ የራስን ግለሰብኣዊ ማንነት ፈልጎ ማግኘትን፣ ኹለተኛ፣ ራስን ፈልጎ የማግኘትን፣ የማወቅን ሒደት እና ሥርዐት የሚወክል ሐረግ ነው፡፡

[55]አባ ኃይለ ሥላሴ ወልደ አማኑኤል፣ ካሴት ቁጥር 4A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

[56]የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ ፲፱፻፺፫፣ ገጽ ፫፻፹፡፡

[57]ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፵፰፣ ገጽ ፬፻፺፪፡፡

[58]በየገዳማቱ የሚፈልቅ፣ ፈውስነት፣ ሕይወትነት ያለው፣ ሕመምተኞችን የሚፈውስና የሚያድን ነው (ተሰማ ፳፻፫፣ ገጽ ፲፪፻፹)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል፣ በጸሎት፣ በመስቀል የተባረከ ውኃ እንደኾነ ይነገራል (የሺጥላ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፳፰)፡፡

መዳኛ እንጂ መቅጫ ወይም መጥፊያ[59] እንዳይደለ ይታመናል፡፡[60] ለዚኽም ይኾናል ብዬ ያሰብኩትን መላምት ላቅርብ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ዐመት ሲሞላው በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቋል፡፡[61] በእርሱ ጥምቀት የአዳምና የዘሩ የዕዳ ደብዳቤ እንደ ተቀደደ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሠርክ ይዘከራል፡፡ ከዚኽ ጊዜ ጀምሮ ይመስለኛል ጠበል የድኅነት አርማ ኾኖ የተተከለው፡፡ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ዮርዳኖስ በሚል ስያሜ የሚጠራው ጠበል መሠረተ ሐሳብም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ከመጠመቁ ጋር የተያያዘ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በእስካኹኑ ጉዞ በተግባር ቤት እና በጠበል የተፈጸሙ የፈውስ ዐይነቶችን ተመልክተናል፡፡ በመጨረሻም በዚኽ ክፍል የማነሣው በመስቀል የተፈጸመን የፈውስ ሒደት ሲኾን፣ ተረኩ የሚከተለው ነው፡፡

> አንድ እግሩ ሽባ የኾነ ሰው ነበር፣ ከሕመሙ የተነሣ እግሩ ይቆረጥ ተባለ፡፡ ኋላም ወደዚኽ ገዳም መጥቶ አባቶች እግሩን በመስቀል ሲያሹለት ተፈውሶ መሔድ ቻለ፤ ከመቆረጥም ዳነ፡፡[62]

በተረኩ እንደ ተነገረው ፈውስ የተከናወነው በመስቀል[63] ነው፡፡ እዚኽ ላይ ስለ መስቀል አንዳንድ ነጥቦችን ማንሣት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ መስቀል በብሉይ ኪዳን የወንጀለኞች መቅጫ[64] ነበር፡፡[65] በሐዲስ ኪዳን ግን እንደ ውኃ (ጠበል) በሙያም፣ በተግባርም፣ በውጤትም ይለወጣል፡፡ ይኽም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበት ወዲኽ እንደ ኾነ ይነገራል፡፡[66] ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በቀኝና በግራ እንደ ተሰቀሉት ወንበዴዎች (ጥጦስና ዳክርስ) ተወንጅሎና ተቀምሮ ነው እንዲሰቀል የታወጀው፡፡[67]
ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው መስቀል ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት በኋላ ሚናው ተለውጧል፡፡ ለዚኽ ነው በሥርዐተ ቅዳሴ መግቢያ ሰዐት (በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት)

59 ፪ኛ ነገ. ፭÷፲፬፡፡ ይኽን ስል፣ በብሉይ ኪዳን ሙሉ በሙሉ ውኃ የጥፋት ምልክት ነው ወደሚል ድምዳሜ ማቅናቴ እንዳልኾነ ይታወቅ፡፡ ምክንያቱም የሦርያው ንጉሥ ንእማን በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ድኗልና፡፡

60 የሺጥላ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፳፱፡፡

61 ሉቃ. ፫÷፳፩-፳፪፡፡

62 አባ ሠረገላ ገብረ ሕይወት፣ ካሴት ቍጥር 5A, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

63 ብርሃኑ፣ ፳፻፪፣ ገጽ ፻፪፡፡ ንግሥት እሌኒ ኪራኮስ በሚባል ሽማግሌ በተነገራት መሠረት መስከረም ዐሥራ ስድስት ቀን ደመራ አስደምራ፣ እጣን አስጭሳ በእግዚአብሔር አመልካችነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል የተቀበረበትን ቦታ አገኘች፡፡ በዚኽም መሠረት መስከረም ዐሥራ ሰባት ቀን ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት ዐሥር ቀን ተገኝቶ ወጥቷል፡፡ በወቅቱ መስቀሉ በርካታ ድውያንን ፈውሷል፡፡

64 ጎርጎርዮስ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፻፬፡፡ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት በፊት መስቀል መቅጫ እንደ ነበር ይነገራል፡፡ ሰውን በስቅላት መቅጣት የተጀመረው በፋርስ ነው፡፡ በፋርስ ሰዎች አምልኮት የመሬት አምላክ Ormazde ይባላል፡፡ ወንጀለኛ በሀገራቸው ሲገኝ ቅጣቱን በመሬት የተቀበለ እንደ ኾነ አምላካቸው እንዳይረክስ ወንጀለኛውን ኹሉ በመስቀል ይሰቅሉት ነበር፡፡

65 ዘዳ. ፳÷፳፫፤ ገላ. ፫÷፲፫፡፡

66 መቃርዮስና ሌሎች፣ ፲፱፻፹፰፣ ገጽ ፺፰፤ ጎርጎርዮስ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፻፬፡፡

67 ማቴ. ፳፯÷፴፰፡፡

“መስቀል አብርሀ በከዋክብት አሰርገወ ሰማየ እመኵሉሰ ፀሐየ አርአየ:: “መስቀል አብርሀ በከዋክብት አሰርገወ ሰማየ” (መስቀል አበራ በኮከቦች ሰማይን ሸለመ (አስጌጠ)፤ ከኹሉም ፀሐይን አሳየ፤ መስቀል አበራ፤ በኮከቦች ሰማይን ሸለመ) እያሉ ምስጋና የሚያቀርቡበት[68] በተመሳሳይ “ኹለቱንም አድሶ አንድ ያደርጋቸው ዘንድ በሥርዐቱ የትእዛዝን ሕግ አጠፋ፤ ርቅንም አደረገ:: በመስቀሉም በአንድ ሥጋው ኹለቱን ወደ እግዚአብሔር አቀረባቸው:: በእርሱም ጥልን አጠፋ”[69] ኹለቱም ሐሳቦች የመስቀል ቀዳሚ ታሪኩ ይኸውም መቅጫ መኾኑ መሻሩን መረዳት ይቻላል::

በደብረ ሊባኖስ በርካታ ድዉያን በመስቀል እየ ታሹ ድነዋል፤ ተፈውሰዋልም:: ይቆረጥ የተባለ እግር ከመቆረጥ ድኖ፣ ሽባነቱ ቀርቶ በሰላም መጓዝ ጀምሯል:: ስለዚኽ መስቀልም በድኅነት ወይም በፈውስ አርማነት የተወከለ ትእምርት ነው:: በአጠቃላይ ከፈውስ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች የገዳሙን ህልውና የመጠበቅ፣ ቅጥሩን የማበጀት ሚና አላቸው:: ለዚኽ ሳይኾን ይቀራል እንደ ሰንደቅ ተተክለው በሚውለበለቡ (በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ርእዮት ጠገግ) ትእምርቶች (ጠበል፣ መስቀል) ተቃኝተዋል::

## ፪.፫ ከስያሜ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች[70]

ስያሜ የአንድ ነገር ምንነት የሚነገርበት ስለ ኾነ ማንነትን ሊገልጽ ወይም ሊቀርጽ ወይም ሊሸከም ይችላል:: የቅድስና ቦታዎች ናቸው የሚባሉ የተለያዩ ሥፍራዎች ቅድስናቸው ከሚገለጽበት መንገድ አንዱ ስያሜ ነው:: ስያሜው በአመዛኙ የህላዌው ዕውቀትና ፍላጎት ማደሪያ እንዲኹም የኃይልና ሥልጣኑም መከሠቻ ይኾናል:: በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከስያሜ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮችን ከስያሜያቸው ተነሥተን ስንመረምራቸው፣ ከተለያዩ ታሪካዊ ክሥተቶች ጋር ወደ ኋለኛው ዘመን ይመልሱናል:: ይኽ ደግሞ ከዚያ ኹነት ተጋሪ እንዲኾኑ ለማድረግ የተሰጡ ያስመስላቸዋል:: በዚኽም የአንድ ነገር መጠሪያ በተለይም በሃማኖታዊ ሕዝባዊ ጥበብ (ፎክሎር) ውስጥ ሥፍራም ምንኛ እንደሚገዝፍ መገንዘብ ይቻላል::

በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይም ኾነ በሐዲስ ኪዳን ከስያሜ ጣጣ ጋር ተያይዞ የሚከሠቱ ማንነታዊ ለውጦች ይስተዋላሉ:: ከብሉይ ኪዳን አብርሃም፣ ሣራ እና ያዕቆብን፤ ከሐዲስ ኪዳን ጴጥሮስና ጳውሎስን ማየቱ በቂ ይመስለኛል:: ስለ ኾነም ስም ከመጠሪያነት በዘለለ ፈርጀ ብዙ ፋይዳዎችን ይጠቀልላል:: ምክንያቱም የስያሜ ጣጣ የብዙ ጉዳዮች ለውጥ ብሎም መከሠቻ ነውና::

[68] ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፺፰፣ ገጽ ፴፯::

[69] ኤፌ ፪÷፲፭-፲፮::

[70] ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፻፷:: ልዕለ ተፈጥሮ ህላዌ በሚገንባቸው ሃይማኖታዊ ተረኮች ውስጥ የሚከናወን ስያሜ በአመዛኙ፣ የህላዌው ዕውቀትና ፍላጎት ማደሪያ፣ የኃይልና ሥልጣኑም መከሠቻ ከመኾን አይዘልም ብሎ ማሰብ ይቻላል::

በገዳሙ ውስጥ የተሰጡ ስሞች፣ ስም ለመስጠት ብቻ የታለሙ ሳይኾን ሌላ ተናባቢ ተረክ እያለመዱ ተደራቢ ግብር እንዲኖራቸው ለማድረግ የታሰበ ይመስለኛል፡፡ የገዳሙን ስያሜዎች በማንሣት ይኽን ጉዳይ ማስረዳት በጎ ይሆናል፡፡ ግራርያ፣ ደብረ አስቦ፣ ዜጋ መል፣ ኤላም እና ደብረ ሊባኖስ የሚሉት ለገዳሙ የተሰጡ መጠሪያ ስሞች ናቸው፡፡ በቅድሚያ ግራርያን እንመልከት፤

> በ፫ ዐ.ም. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በስደት ወደ ሀገራችን መጥታ በዚኽ ዋሻ ስታርፍ ግራር ተመለከተች፡፡ በዚያ ግራር ሥር ሔደን እንረፍ፣ እንጠለል አለች፡፡ ተጠለሉበትም፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የቦታዋ ስም ግራርያ ተባለ፡፡[71]

ድንግል ማርያም በሥፍራው በተመለከተችው ግራር ምክንያት ቦታው “ግራርያ” የሚል ስያሜ እንደ ተሰጠው እንረዳለን፡፡ ግራር በቁሙ ጥላ ወይም ከለላ መሰል ቅርጽ አለው፡፡ አንድም ግራር ከፀሐይና ከሐሩር ለመጠለያነት ያገለግላል፤ አንድም ለመሰብሰቢያነት ይበጃል፡፡ ይኽን ትርጓሜ ልያዝና የተረኩ በዚህ ጠገግ መተረክ ገዳሙ ለሰብኣውያን ጥላ፣ መሰብሰቢያ እንደ ኾነ ለማጠየቅ ይመስለኛል፡፡ “ደብረ አስቦ” ሌላኛው ስም ነው፡፡ በዚኽ ዙሪያ ያናገርኳቸው የቤተ መዘክሩ ሓላፊ ይኽን ብለዋል፤ “ገዳሙ ደብረ አስቦ እየተባለ ይጠራል፡፡ የዋጋ ተራራ ማለት ሲኾን የሰየመውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የድካምህ ዋጋ፣ የስምህ መጠሪያ ይኹንልህ ብሏቸዋል”[72]

አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተለያዩ የሀገሪቱን ክፍሎች በተጋድሎ እንዳቀኑ ገድላቸው ያስረዳል፡፡ በአባታቸው ቤት ፳፪ ዐመት፣ በከታታ ሦስት ዐመታት፣ በዊፋት ዘጠኝ ወራት፣ በዳሞት ፲፪ ዐመት፣ በዐምሐራ ፲ ዐመታት፣ በሐይቅ ፲ ዐመታት፣ በደብረ ዳሞ ፲፪ ዐመታት፣ የትግሬን ገዳማት በመጎብኘት አንድ ዐመት፣ በዳዳ አንድ ወር፣ በደብረ አስቦ ፳፱ ዐመታት ፲ ወራት ከ፲ ቀናት ያኽል ቆይተዋል፡፡[73] በጥቅሉ የተለያዩ አውራጃዎችን እያቋረጡና እያካለሉ ከ፸፯ ዐመታት በላይ እንደ ተጋደሉ እንረዳለን፡፡ ወደ ገዳሙም በ፲፪፻፸፯ ዐ.ም. እንደገቡ ይነገራል፡፡[74]

አንድ ተጋዳሊ ለተጋድሎ ከታጨበት ጊዜ አንሥቶ የተለያዩ አውራጃዎችን ይሻገራል፤ በድንበር አስማሪዎች የተበጀውን ቅጥር ጥሶ ይዘልቃል፤ በእያንዳንዱም የተጋድሎ ሕይወት የፈጣሪው ረድኤት ፈጽሞ አይለየውም፡፡ በመጨረሻም ተጋድሎውን በድል ይቋጫል፤ ዋጋም ያገኛል፡፡ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትም የተጋድሎ ብሂል ከዚኽ አይወጣም፤ ይልቁንም በዚሁ ሥር አዳሪ ነው እንጂ፡፡ ስለኾነም መላ ዘመናቸውን

[71]አባ ኪዳነ ማርያም ብርሃን፣ ካሴት ቁጥር 3A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

[72]ዝኒ ከማሁ፡፡

[73]ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱:፵፱÷፲፩-፲፰፡፡

[74]መምህር ኃይለ ሚካኤል ወልደ አምላክና ሌሎች፣ ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም.፤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም፣ ፰፡፡

ለፈጸሙት ተጋድሎ በድል አክሊልነት የተከፈለ ነው ማለት ይቻላል፤ የ"ዋጋ ተራራ" መባሉም ለዚኽ ነው።

በሌላ መልኩ ግራርያ በድንግል ማርያም፣ ደብረ ዐስቦ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጡ ስያሜዎች ናቸው። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ እንደ ኾነ የታመነ ነው። ድንግል ማርያምም ከዐለም ሴቶች ኹሉ የተለየች ናት። ያለ ወንድ በመፅነሷ፣ በድንግልና በመውለዷ፣ ከውርስ ኃጢኣት ነጻ በመኾኗ ስሟ ሠርክ ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎ ይጠራል። ስለዚኽ ኹለቱ ስያሜዎች በእነርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም) እንደ ተሰየሙ መተረኩ ሥፍራው በእናትና ልጁ የተባረከና የተቀደሰ መኾኑን ለማጽናት፤ ታላቅነቱን ለማግዘፍና ጥንታዊነቱን ለመዘከር የተገለገሉበት ይኾናል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው የሚነሣ ጉዳይ በተረኩ የስያሜ ሒደት ከዚህ ቀደም ካየናቸው የተለየ ስለኾነ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

> ከዚያም ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤልን ዝግ ብለህ ና አትቸኩል አለው። ከዚህ አባባል ገዳሙ "ዝግ ደም፣ ዝግ ደም" የሚለውን ቀዳሚ ስም ያዘ። ከጊዜ ወደ ጊዜም የፊደል ለውጥ እየተደረገበት "ዜጋ ምኤል" ተባለ። ከዚያም "ዜጋ መል" ተብሎ መጠራት ጀመረ።[75]

በተረኩ ከቅዱስ ሚካኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ንግግር ውስጥ ለሥፍራው "ዝግ ደም" የሚል ስያሜ እንደ ወጣለት፣ ኋላም የፊደል ለውጥ እየ ተደረገበት ዜጋ ምኤል እንደ ተባለ እንረዳለን። ተለዋጩ ስም ከቀዳሚው እጅግ የሚሰፋ ይመስለኛል። ስሙ ከኹለት ቃላት የተገነባ ነው፤ "ዜጋ እና ምኤል" ከሚሉት። "ዜጋ" ታዛዥ፣ ዜጋ መኾን፣ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር፣ ወዘተ... ማለት ነው።[76] "ም" በተረኩም እንደ ተገለጸው ከፊደል ለውጥ ጋር ተያይዞ የመጣ ሊኾን ይችላል። በራሱም ኾነ ሲገጥም ፍቺ አይሰጥም። ስለዚህ "ኤል" ወደሚለው የሚያደላ ይመስላልና እርሱን እንመልከት። "ኤል" ስመ አምላክ ሲኾን ቅጥያ እየ ኾነም በመላእክት ስም ላይ ይደረባል።[77] **ለምሳሌ፣ ሚካኤል የሚለውን ስም እንመልከት። ሚካኤል ትርጓሜው እንደ እግዚአብሔር ማን ነው? ማለት ነው።**[78]

[75] አባ ወልደ ገብርኤል ምሕረቱ፣ ካሴት ቁጥር 2A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም

[76] ደስታ፣ ፲፱፻፺፰፣ ገጽ ፬፻፸፱፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ማዕከል፣ ፲፱፻፺፫፣ ገጽ ፬፻፹፫።

[77] ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፺፰፣ ገጽ ፩፻፳፩፤ በላይ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፩፻፳፱።

[78] **የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፹፱።**

ከዚኽ በመነሣት ኹለቱን ቃላት ገጥመን ስናነበው የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚል አንድምታዊ ፍቺን ይፈጥራል፡፡ ስለ ኾነም ተረኩ፣ ገዳሙ የእግዚአብሔር ሕዝብ መኖሪያ እንደ ኾነ የማጠየቅ ግብር አለው ማለት ይቻላል፡፡

“ዜጋ ምኤል” እየ ቆየ ሲሔድ “ዜጋ መል”ም ተብሏል፡፡ ገዳሙ ልሳነ ደብረ ሊባኖስ በሚል ርእስ ባሳተመው ዐጭር መጽሔት ውስጥ “ዜጋ መል” አየር ንብረቷ የተመቸ፣ ተስማሚ፣ የሚያስደስት… የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡ ይኽም ቢኾን የገዳሙን ታላቅነት፣ ለምነት፣ በገዳሙ የሚገኘውን መንፈሳዊና ሥነ ልቡናዊ ርካታ ከመትከል ጋር የተያያዘ ነው፡፡
ሌላው “ኤላም” ነው፡፡ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አፅም ከደብረ ዐስቦ ዋሻ ወደ ኤላም ፈልሷል፡፡ በኤላምም ለዐርባ ዐመታት ያኽል ተቀምጧል፡፡ አቡነ ሊባኖስም በኤላም እንደ ተቀመጡ ይነገራል፡፡[79] ከዚኽ ስያሜ ጋር በተያያዘ ከገዳሙ አበ ምኔት የተነገረኝን ተረክ ላቅርብ፤ “ገዳሙ ኤላም የሚል መጠሪያም አለው:: ስያሜውን የሰጡት ጻድቁ አቡነ ዮሐንስ ከማ ናቸው፡፡ አቡነ ዮሐንስ ከማ የአባታችን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመንፈስ ልጅ ናቸው (ጸባቴ[80] አባ ወልደ ማርያም አድማሱ፣ ካሴት ቁጥር 7A, መጋቢት ፳፻፯ ዓ.ም)፡፡

እንደ ኪዳነ ወልድ ትርጉም “ኤላም” ደጀ ሰላም የሚለውን ፍቺ ይይዛል፡፡[81] ደጀ ሰላም አንድም የበረከት ቦታ ወይም ሥፍራ፤ አንድም ሠፈረ ሰላም (ሰላም የሠፈነበት) የሰላም ደጅ ማለት ነው፡፡ በዚኹ መንገድ እንየውና ገዳሙ በበረከት የተከበበ መኾኑን ማለትም፣ በቀን (፲፪ ሰዐት) አንድ ጊዜ ብቻ ተመግቦ መዋል መቻሉ በገዳሙ ረሀብ ድል መመታቱን እና ጸጋና በረከት የሞላበት፤ በሰላምና በጸጥታ የተቃኘ እንደ ኾነም እንረዳለን፡፡

አምስተኛውና የመጨረሻው ስያሜ “ደብረ ሊባኖስ” የሚለው ነው፡፡ ደብረ ሊባኖስ የሚለው መጠሪያ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ (፲፬፻፳፮-፲፬፻፷) የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ አቡነ ሊባኖስ ቀድሞ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ገዳሙ ዕድል ፈንታቸው እንዳልኾነ ነግሯቸዋል (ይኽ ጉዳይ በመግቢያው ውስጥ ሠፍሯል)፡፡ በዚያው መጽናትን ሽተው ስለ ድካማቸው ቢማጸኑም ቦታው ለዘለዐለም በስማቸው እንደሚጠራ ያረጋግጥላቸዋል፤ ጊዜው ሲደርስም ኪዳኑ ይጸናል፡፡ የስያሜው ሒደት በተረኩ የሚገለፀውን ያህል በጽሑፋዊ መረጃም ተጠቅሶ

[79] ደብረ ሊባኖስ ገዳም፣ ፳፻፮፣ ገጽ ፯፡፡

[80] ጸባቴ አባ ወልደ ማርያም አድማሱ፣ ካሴት ቁጥር 7A, መጋቢት ፳፻፯ ዓ.ም፡፡ ለደብረ ሊባኖስ ገዳም አበ ምኔት የሚሰጥ የማዕረግ ስም ሲኾን የሚያገለግለውም ለዚኽ ገዳም ብቻ ነው፡፡

[81] ኪዳነ ወልድ ፲፱፻፹፰፣ ገጽ ፪፻፳፫፡፡

ይገኛል፡፡ “ዐፄ ዘርአ ያዕቆብ ድል አድርገው ሲመለሱ[82]ይኽን ድል ለሰጠኝ ለአባቴ ለተክለ ሃይማኖት ምስጋና ይኹን፡፡ የገዳሙም መጠሪያ ስም ደብረ ሊባኖስ ይባል፤ ብለው ሰይመውታል” ይላል ያልታተመው የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል፡፡ ስሙም በዚያው ጸና፤ በሌላ አልተተካም፤ አልተለወጠም፡፡

በሌላ መልኩ “ደብረ ሊባኖስ” የሚለውን መጠሪያ ከፋፍሎ መመልከቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ “ደብር” በከፍታ ላይ ያለ ተራራ ሲኾን[83] “ሊባኖስ” ደግሞ ከገሊላ በስተሰሜንና ከፊንቄ[84] በስተምሥራቅ የሚገኝ ተራራማ ሀገር ነው፡፡[85] የሊባኖስ ተራራማ ሀገር በዝግባ ዛፍ የታወቀ በመኾኑ ሰሎሞን ለቤተ መቅደሱ ሥራ እንጨት ከዚያ ያስመጣ ነበር፡፡[86] ኹለቱም ቃላት ተራራን ገላጭ ናቸው፡፡ “ደብረ ሲና”፣ “ደብረ ታቦር”፣ “ደብረ ዘይት”፣ ወዘተ... እንዲባል፡፡ ተራራን በተመለከተ ቴዎድሮስ[87] በግርጌ ማስታወሻ ያሰፈረውን እንዳለ አቅርቤዋለሁ፡፡

> ተራራ በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ታላላቅ ተአምራት የሚከሠቱበትና ከፍ ያሉ ተግባራት የሚከናወኑበት ምርጥ “ሥፍራ” ነው፡፡ ሙሴ በሲና ተራራ ሕግና ትእዛዝን ከእግዚአብሔር ተቀብሏል፡፡[88] ተራራ አብርሃም በልጁ የተፈተነበት፣ ፍጹም ታዛዥነቱ የታየበት፣ የእግዚአብሔር ምሕረት በፈንታው የተገለጠበት ሥፍራ ነው፡፡[89] ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ ስብከቱ እጅግ ይታወቃል። ኤልያስና ሙሴ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተገልጠው የታዩት በረጅም ተራራ ላይ ነው፡፡[90] ወዘተ ... ፡፡

[82]የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ለክርስትና ሕይወት ውስብስብ እንደ ነበር ታሪክ ይዘክረዋል፡፡ በወቅቱ በምሥራቅ ይኖሩ የነበሩ እስላሞች አጋጣሚን በመጠቀም የክርስትናን መስፋፋት ለመግታት ያልተቆጠበ ጥረት ያደረጉ ነበር፡፡ ለዚህም የአዳሉ ንጉሥ በድላይ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይኽ ገዢ የደጋውን ክርስቲያናዊ ክፍል በክረምት፣ በበዐላትና በአጽዋማት ወራት እያጠቃ አብያተ ክርስቲያናትን ያቃጥላል፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ ያስገድዳል፤ እምቢ ያሉትን ይገድላል፡፡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ይኽን ድንገተኛ አደጋ ለመከላከል ጨዋ የሚባለውን ሠራዊት በየሀገሩ አሥፍሮ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ይኽም ኾኖ አደጋው ይገታ ዘንድ አልተቻለም፡፡ ይልቁንም በአንድ ወቅት ለገና በዐል አካባቢ ሠራዊቱ በዐሉን ለማክበር በየቀበሌው በተበተነበት ወቅት እስከ ፈጠጋር ዘልቆ ሕዝበ ክርስቲያንን ገደለ፤ አብያተ ክርስቲያንን አቃጠለ፡፡ በዚኽም ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ እጅጉን ተበሳጭቶ ዐመት በዐሉንም ሳይውል ጥቂት ወታደሮችን ብቻ ይዞ ወደ ፈጠጋር አቀና/ገሰገሰ፡፡ ከአዋሽ ማዶ ጦርነት ገጥሞ በድላይን የልደት ዕለት (ገና) ድል አደረገው፤ ገደለውም፡፡ የብረት ለምዱንና የክብር ልብሱን ማረከ፡፡ ለምዱን ለደብረ ወርቅ ማርያም፣ የክብር ልብሱን ለመርጡለ ማርያም ጎጃም ሰጠ፡፡ ኹለቱም እስከ ዛሬ በሥፍራዎቹ ይገኛሉ (ሥርግው፣ ፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፻፶፰)፡፡

[83]ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፵፰፣ ገጽ ፫፻፴፮፡፡

[84]ከገሊላ ወደ ሰሜን እስከ ፪፻ ኪ.ሜ ያኽል ስፋት ያለው በታላቁ ባሕር ዳር ያለ ሀገር ነው፡፡ ዋና ከተማዎቹ በንግድ፣ በኪነ ጥበብና በሥነ ጽሑፍ የታወቁ ጢሮስና ሲዶና ናቸው (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ፲፱፻፺፪፣ ገጽ ፪፻፸፫)፡፡

[85]ዘዳ. ፩÷፯፡፡

[86]የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ፲፱፻፺፪፡፲፮፤ ፩ኛ ነገ ፬÷፴፫፡፡

[87]ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፻፲፯፡፡

[88]ዘጸ. ፳፬፡፡

[89]ዘፍ. ፳፪፡፡

[90]ማር ፱÷ ፩-፰፡፡

ከዚኽ የምንረዳው ተራራ ከአምልኮ ሥርዐት ጋር የሚያያዝና አምላካዊ (መለኮታዊ) ተአምራት ክሡት የሚኾኑበት ሥፍራ እንደ ኾነ ነው። በዚኽም ደብረ ሊባኖስ መባሉ ከላይ እንደ ተጠቀሱት ቦታዎች መሰል ተአምራት የሚታይበት መኾኑን ለማመልከት ነው ብሎ ማጠቃለል የሚቻል ይመስለኛል።

## ፪.፬ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች

ለዚኽ ክፍል የሚበጁና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ የተለያዩ ተረኮች ተፈትሸዋል። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ገዳሙ ከመምጣታቸው በፊት (ከ፲፪፻፳፯ ዐ.ም) እና በኋላ ከፈርጀ ብዙ ተጋድሎአቸው ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች አሉ። ይኽም ለተጋድሎ ከተጠሩበት ጊዜ ይነሣል።

የገድል ጥሪ የሚታዊው ሥርዐት ወይም ጉዞ ቀዳሚ ምዕራፍ ሲኾን በአንድ ጊዜ ኹለት ጉዳዮችን ዐቅፎ ይይዛል፡ ቀዳሚው ዘወትራዊው ዐለም ሲኾን ሌላው ደግሞ ጥሪውን ራሱን ነው። ዘወትራዊው ዐለም ጥሪው እንደ መብረቅ ብልጭታ ተግ የሚልበት፣ ሠርካዊው ኑሮ የሚከናወንበት ነባሩና ተለምዷዊው ዐለም ሲኾን ጥሪው ደግሞ ተጋዳሊውን ከማኅበሩ አቋም የሚለይ ወደ ዐዲስ እና እጅግ ወደ ተለየ ዐለም የሚያመራ የማንቂያና የመቀስቀሻ ደወል ነው።[91] አስቀድሞ ለገድል የሚታጩ ተጋዳልያን የፈጣሪ ረድኤት ስለ ማይለያቸው ከሚመጣው መዐት ይተርፋሉ፤ እንደውም ለመዐቱ መቀልበስ ሰበብ ይኾናሉ፤ ጊዜያቸው እስኪደርስ ሊሰደዱም ሊሰወሩም ይችላሉ። ለተጋዳሊነት ታጭተው የተወለዱ እኒኽ ሕፃናት ወደ ሙሉ ሰውነት ተሸጋግረው ለተጋድሎ ከመጠራታቸው በፊት ባለው የልጅነትና፣ የታዳጊነት ዕድሜያቸው ተአምራትን በመፈጸም የነገ ማንነታቸውን ይጠቁማሉ። ለምሳሌ በገድለ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ እንደ ተገለጸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሕፃንነት እጃቸው ያረፈበት እፍኝ ዱቄት፣ ቁንጣሪ ቅቤ ተዝቆ የማያልቅ ክምር ይወጣዋል።[92]
አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከላይ ስለ ተጋዳሊ ጥሪ ባነሣሁት መሠረት ለታላቅ ተጋድሎ[93]

---

[91]ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩:፫።

[92]ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱:፲፯÷፳፱-፶፫።

[93]"ተጋድሎ" ወይም "ገድል" ሰማዕታት ስለ ክርስቶስ እጅ እግራቸውን ለሥለት ዐይናቸውን ለፍላት ሰጥተው በሰውነታቸው የፈጸሙት ትግልና ግድያ። ጻድቃን የመዐልት ሐሩር የሌሊት ቁር ታግሰው ዳዋ ለብሰው ደንጊያ ተንተርሰው ጤዛ ልሰው ያደረጉት ስግደት ጾም ጸሎት ትሩፋት መልካም ሥራ ኹሉ (ደስታ፣ ፲፱፻፵፰፣ ገጽ ፪፻፴፮) በሚል ታትቷል። "ተጋድሎ" ትግልና ውጊያ፣ "ድልና አክሊል እስኪያገኙ" ድረስ የሚወጡት ግዳጅ፣ የሚቀበሉት መከራ ጭምር ነው። ተጋድሎ መንፈሳዊ/ሃይማኖታዊ፣ ሥጋዊ/ዐለማዊ ሊኾን ይችላል። እንደ ተጋድሎው ዐይነት የተጋድሎውም ዐላማና ውጤት፣ ከተጋድሎ ተይዞ የሚወጣው በረከት መንፈሳዊ አልያም ቁሳዊ በረከት ይለያያል (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፪፻፳፫-፪፻፳፯)።

የተለዩና የታጩ ተጋዳሊ[94] ናቸው፡፡

> አውሬ ማደን አንድም ለሕዝባውያን፤ አንድም ከእምነት ለወጡ ለአረማውያን ነው፡፡ ለካህናትስ ሕዝብ መምከር፣ ማስተማር፣ መመለስ እንጂ አውሬ ማደን ተገቢ ሥራ አይደለም፤ አላቸው፡፡ ይኽን እንዳላቸው ጌታችን ከእናቱ ከድንግል ማርያም፣ ከሐዋርያት ጋር በአካለ ሥጋ እንዳለ በቅዱስ ሚካኤል ክንፍ ላይ ተገልጾ ታያቸው፡፡ ያን ጊዜ ፍግም ብለው ወደቁ፡፡ በቅዱስ ሚካኤል አማካይነት በፍሥሐ ጽዮን ፈንታ ተክለ ሃይማኖት ብዬ ዐዲስ ስም አውጥቼልሃለኹ፡፡ ከእነርሱ በምንም አታንስም፡፡ በወንጌል አገልግሎት ሹሜሃለኹ ብሎ ከንፈራቸውንና ግንባራቸውን ስሞ ዐረገ፡፡[95]

ከተረኩ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለአደን በወጡበት ወቅት ለተጋድሎ መጠራታቸውን፣ መታጨታቸውን እንረዳለን፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ትምህርት ለተጋድሎ የታለሙ ተጋዳልያን ከተለያየ መስክ ወይም ሙያ ይጠራሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ቅዱስ ጴጥሮስና ወንድሙ እንድርያስ ከዐሣ አጥማጅነት ተጠርተዋል፡፡[96] ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት ማሳደድ በወጣበት በደማስቆ ሜዳ፡፡[97] ነቢዩ ኤልሳዕን ያየን እንደ ኾነ በዐሥራ ኹለት ጥማድ በሬ በማረስ ላይ ሳለ በኤልያስ ተከተለኝ ተብሏል፡፡[98] ብሂሎቹ ለተጋድሎ የሚለዩ ተጋዳልያን ከልዩ ልዩ ሙያና መስክ መኾኑን ያስገነዝቡናል፡፡ በመጨረሻም ከተጠሩበት ጊዜ አንሥቶ ለፈጸሙት ተጋድሎ ዋጋ ይከፈላቸዋል፡፡ ብድራቱም ለአካባቢያቸው፣ ለወገኖቻቸው፣ ለሀገራቸው ሲረዝም ለዐለም ሊኾን ይችላል፡፡ የአቡነ ተክለ ሃማኖት ዕጣ ፈንታም ከዚኹ ሚታዊ ብሂል የወጣ አይደለም፡፡

ዐሣ አጥማጁ ጴጥሮስ "ከእንግዲኽ ሰው ታጠምዳለኽ" እንደ ተባለ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትም እንስሳትን የማደን ግብር ሰው በማደን ይተካል፡፡ ይኽ መታጨት በንጽረተ ዐለምም ይኹን በፍልስፍና ፈለግ ከቀዳሚው ማንነት ፈጽሞ የተለየ ይኾናል፡፡ ነባሩ የማንነት ይዞታ በዐዲሱ ይለወጣል፡፡ ለዚኽም ነው "አውሬ ማደን አንድም ለሕዝባውያን፤ አንድም ከእምነት ለወጡ አረማውያን ነው፤ ለካህናትስ ሕዝብ መምከር፣ ማስተማር፣ መመለስ እንጂ ..." የተባለው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያምና ከሐዋርያት

[94]"ተጋዳሊ" የሚጋደል፤ ተጋዳይ፡፡ ገድለኛ፤ መንፈሳዊ ዐርበኛ (ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፵፰፣ ገጽ ፫፻፩)፡፡ ተጋዳሊው የገድሉ ባለቤት ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጋዳሊ እንደ የዘመኑና እንደ የልማዱ ፍቺው ይለዋወጣል፡፡ በብሉይ ሚቶሎጂ ተጋዳሊነት የዕጣ ፈንታ ጉዳይ ነው፡፡ ተጋዳሊው ይመረጣል፤ በመለኮት ይቀባል፤ የፈጣሪ እገዛም አይለየውም፡፡ በዐዲስ የሚት ልማድ ተጋዳሊ በሌላ ኃይል አይመረጥም፤ አይወለድም፤ ራሱን በራሱ ለዚያ ዐይነቱ ማዕረግ ያበቃል (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፪፻፰)፡፡

[95]አባ ኪዳነ ማርያም ብርሃን፣ ካሴት ቁጥር 3A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

[96]ሉቃ ፫÷፩-፲፩፡፡

[97]የሐዋ. ሥራ ፱÷፩-፴፡፡

[98]፩ኛ ነገ. ፲፱÷፲፱-፳፩፡፡

ጋር ኾኖ በቅዱስ ሚካኤል ክንፍ ላይ ይገለጽላቸዋል፡፡ በአብዛኛው በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኙ ተረኮች ይኽን መሰል ብሂል አያጣቸውም፡፡ ተጋዳሊው ወይም ተጋዳሊዋ ለተጋድሎ ሲጠሩ በልዕለ ተፈጥሮ ኃይላት ይጎበኛሉ፡፡ ስለኾነም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከፊት የሚጠብቃቸውን ቅጥር ለመዝለቅ፣ ምስለ አጋንንትን ድል ለማድረግና ለማፈራረስ፣ የማይደፈሩ ቀጠናዎችን ለማለፍ፣ የእግዚአብሔር፣ የድንግል ማርያምና የመላእክቱ ረድኤት ሠርክ እንደማይለያቸው ያጠይቃል፡፡

በሌላ በኩል ፍሥሐ ጽዮን[99] የሚለው ስም በተክለ ሃይማኖት[100] ይተካል፡፡ ቀደም ብዬ ስያሜን በተመለከትኩበት ክፍል ስያሜ የአንድ ነገር ምንነት የሚነገርበት በመኾኑ ማንነትን ሊገልጽ ወይም ሊቀርጽ እንደሚችል ጠቁሜ ነበር፡፡ ስለዚኽ የስም ለውጥ እንዲኹ የሚከናወን እንዳልኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይልቁንም ከለውጡ ጋር የሚያስከትለው አንዳች ፋይዳ ይኖራል፡፡ ተክለ ሃይማኖት የሚለው ስም ከፍሥሐ ጽዮን በሙያ የሚልቅ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ስሙ በተክለ ሃይማኖት ከተተካ በኋላ የተጋድሎ ምዕራፍ ይገለጣል፡፡ ከበቀሉበት ማኅበረሰብና አካባቢ አንሥቶ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለተጋድሎ ይሰማራሉ፡፡ በፍሥሐ ጽዮን ዘመን ግን ከእናትና አባታቸው ጋር ነበሩ (ነገር ግን ያኔም ጥቃቅን ገቢረ ተአምራትን ያደርጉ ነበር)፡፡ ስለዚኽ የስም ለውጡ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን የወደፊት የተጋድሎ መልክ ጠቋሚ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በፈጣሪ ፍቃድና ፍላጎት ወደራሱ ማኅደር ውስጥ አሻግሯቸዋልና፡፡ ስለኾነም መንገዳቸውም፣ አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸውም በእግዚአብሔር ይወሰናል፤ ይቀናልም፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "በወንጌል አገልግሎት ሹሜሃለኹ ብሎ ከንፈራቸውንና ግንባራቸውን ስሞ …" የሚለው ሌላኛው ነጥብ ነው፡፡ በቅድሚያ ከከንፈር መሳም ጋር በተያያዘ መላምቴን ልሰንዝር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በተነሣ በኀምሳኛው ቀን ለሐዋርያቱ መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው፡፡ ሐዋርያቱም በሀገሩ ቋንቋ ኹሉ ተናገሩ፡፡ ነገረ ወንጌልን ከጥግ እስከ ጥግ አዳረሱ፡፡ ከዚያን በፊት ግን እጅግ በፍርሃት ነበሩ፡፡ የሚያጸና፣ የሚያበረታ መንፈስ አልተሰጣቸውምና፡፡ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ነገርም ከዚኽ የሚወጣ አይመስለኝም፡፡ ይልቁንም የታጩት ለወንጌል አገልግሎት ነውና ለነገረ ወንጌል መቀልጠፍ አንደበትን ከመሳል (ርቱዕ ከማድረግ) ጋር ይያያዛል፡፡ ሐዋርያት አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት መንፈስ ቅዱስ መላባቸው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በስዕመቱ ክዋኔ የተጋድሎ ብሂል ኩብርታት ጋር አንድም በአፍኣ፤ አንድም በልቡና (በውሳጤ) ሰረፀባቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በወጡበት አትርፈዋል፤ ማኅበረ አጋንንትን ቀጥቅጠዋል፤ አድቅቀዋል፤ ሙት አንሥተዋል፤

[99]ከቤተ መቅደስ በደረሱ ጊዜ አጥምቀው ስሙን ፍሥሐ ጽዮን አሉት፡፡ ትርጓሜውም የጽዮን ደስታ ማለት ነው፡፡ ባማረ በተወደደ ትምህርቱ ቤተ ክርስቲያንን (ምእመናንን) ደስ ያሰኛልና (ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱፣ ገጽ ፲፮÷፬-፯)፡፡

[100]ስምህ "ፍሥሐ ጽዮን" አይኹን፡፡ "ተክለ ሃይማኖት" ይኹን እንጂ፡፡ ትርጓሜውም "ተክለ አብ፣ ተክለ ወልድ፣ ተክለ መንፈስ ቅዱስ" ማለት ነው (ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣፲፱፻፹፱፣ ገጽ ፳፯÷፵፱)፡፡ ለውጡ ከቀዳሚው ስም በሙያም በዐላማም ይልቃል፤ ይረቃል፡፡

ድዉያንን ፈውሰዋል፤ በመጨረሻም ከድል ጋር ተመልሰዋል፡፡[101]

የግንባራቸው መሳም ደግሞ በማኅተምነት የሚፈረጅ ትእምርት ሊኾን ይችላል፡፡ ከስዕመቱ በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከቡልጋ አንሥተው ወላይታ ድረስ ይዘምታሉ፡፡ በሔዱበትም በርካታ የሚባሉ ርኵሣን መናፍስት (አጋንንት) ይገጥማቸዋል፡፡ እኒህኽ መናፍስትም ከሩቅ ባዩዋቸው ጊዜ "ይኼን ሰው መልሱልን፤ ሸዋን ተውንልኽ ከዚኽ ልታጠፋን ስለምን መጣኽ; እያሉ እንደሚጮሁ" ገድላቸው ይዘክራል፡፡[102] ስለዚኽ ግንባራቸውን መሳማቸው በሚያቋርጡት ዳር ድንበር፣ በሚዘልቁት ቀጠና ኹሉ ኃይለ አጋንንትን ከሩቅ እያነደዱ እንዲፈጁ የተለጠፈ ወይን የተነደፈ ማኅተም ነው ብሎ መተርጐም ይቻል ይኾናል፡፡

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ጅማሮ ቡልጋ፣ ሲሻገርም ዳሞት (ወላይታ) ድረስ ዘልቋል፡፡ በዚኽም በመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ረድኤት አብያተ ጣዖታትን ያፈራርሳሉ፤ ሕዝቡንም አስተምረው ያጠምቃሉ፡፡ ከዚኽ ሐሳብ ጋር የሚወግን ማሔጃ ላንሣ፤

> ምትሃተኞችም በእሳት ውስጥ ገብተው ይዘፍኑ ነበር፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እሳት ውስጥ ባሉት ምትሃተኞች ላይ ሲያማትቡ አጋንንቱ ለቋቸው ሔደ፡፡ ያነደዱት እሳትም መልሶ እነርሱኑ በላቸው፤ ፈጃቸው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ግን በመንፈሳዊ ኃይል ደቀ መዛሙርቶቻቸውን በእሳቱ ዙሪያ አስከብበው ጸሎት እየ ጸለዩ፣ መዝሙር እየ ዘመሩ እሳቱ ውስጥ ይመላለሱ ነበር፡፡[103]

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በማማተብ (በትእምርተ መስቀል) አጋንንትን እንዳባረሩ በተረኩ ተገልጿል፡፡ ከፈውስ ጋር በተያያዘ መስቀልን የተመለከተ ሐሳብ በሌላ ሥፍራ ተጠቅሶ ነበር፡፡ ያን ሐሳብ ከዚኽ ጋር አዋግኖ ማየት ይቻላል፡፡ ከመስቀል ወይም ከማማተብ ጋር የተያያዘው ሐሳብ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የሚጠራው ቃላዊ ተረክ አለ፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አንድም በመማተብ አጋንንት ይወጣሉ፤ ይርቃሉ፤ ተብሎ ይታመናል፤ አንድም እያንዳንዱ ሥርዐተ ክዋኔ በትእምርተ መስቀል በማማተብ ነው የሚጀምረው፡፡ የዚኽ ቃላዊ ተረክ መሠረተ ሐሳብ ካነሣሁት ጋር ይኅራበታል፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ምትሃተኞቹ በእሳት ውስጥ ሲዘፍኑ ያማትቡባቸዋል፡፡ ወዲያውኑ አጋንንቱ እንደሚለቃቸው በተረኩ ተነግሯል፡፡ እነርሱም ቀልለው ባነደዱትና በድኙ ባንበለበሉት እሳት መልሰው ይበላሉ፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ግን ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር በነበልባሉ መሐል ቆመው ይጸልያሉ፤ ይዘምራሉ፡፡ ሠለስቱ ደቂቅን ወደ ነበልባሉ የከተቷቸውን ሰዎች ፍሙ ሲፈጃቸው፣ እነርሱ ግን በእሳቱ መሐል ኾነው ይጸልዩ፣

[101]ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱:፴፯÷፱-፻፴፪፤ ፴፯÷፹-፺፫፤ ፶÷፪፤ ፶፹÷፷፤ ፶፩÷፩፡፡

[102]ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ፲፱፻፹፱:፴፩÷፻፯-፻፰፡፡

[103]መምህር ኃይለ ሚካኤል ወልደ አምላክ፣ ካሴት ቍጥር 1A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

ይዘምሩ ነበር፡፡[104] ሐማም መርዶክዮስን ለመስቀል ባዘጋጀው ግንድ (መስቀል) ላይ መልሶ ራሱ መሰቀሉም እንዲኽ[105] በዐፄ ይኵኖ አምላክ (፲፪፻፷፫-፲፪፻፸፯) ዘመነ መንግሥት ከግብጽ ተሹሞ የመጣ ጳጳስ አልነበረም፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ዲቁናና ቅስና የሾሟቸው አቡነ ጌርሎስ (ቄርሎስ) በ፲፪፻፶ ገደማ ካረፉ በኋላ የጳጳሳት መምጣት በመሐል ተቋርጦ ነበር፡፡ ዐፄ ይኵኖ አምላክ ጳጳስ ለማስመጣት ከግብጽ ሡልጣን ከሩቅና ዐዲስ ባይባር ጋር በየመኑ ሡልጣን በሐምዳኒድ በኩል ከ፲፪፻፸፬ ዐ.ም. ጀምሮ ይጻጻፉ እንደ ነበር ይነገራል፡፡ ነገር ግን በይፋት በኩል ያለውን የአዳል እስልምናን ንቅናቄ በመደገፍ ሡልጣኑ ጳጳስ ተሹሞ እንዲመጣ አልፈቀደም፡፡ በዚኽም ዐፄ ይኵኖ አምላክ ዐይናቸውን ወደ ሦርያ አዙረውት እንደ ነበር በታሪክ ተሰንዷል፡፡[106]

በዚህ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ በተጋድሎ ላይ የነበሩት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትና በሞተለሚ ጊዜ የጠፉትንም ለመተካት ታቦት የሚባርክላቸው ጳጳስ ማግኘት አልተቻላቸውም፡፡

ያን ጊዜ እኔ አንተን ሹሜሃለኹ፤ ብሎ አምላካችን በቃል ነገራቸው፡፡ እንደ ነገራቸውም ቅዱስ ሚካኤል ከሰማይ መስቀሉን መባረኪያ፣ መጽሐፉን ይዞላቸው መጥቶ ያንን ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ኾነው አክብረውታል፡፡[107]

ከተረኩ እንግዳና ያልተለመደ ኹነት እናገኛለን፡፡ እርሱም የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ማዕረገ ጵጵስና ቀጥታ ከኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጳጳሳት ማዕረገ ጵጵስናን የሚቀበሉት ከሊቃነ ጳጳሳት እንደ ኾነ ተደንግጓል፡፡[108] ስለዚኽ ክዋኔው ተጽፎ ከሚገኘው መርሕ ይወጣል፡፡ ይኽ ማለት ግን በተረኩ እንደ ተነገረው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎች ጳጳሳት ተሹመው በማያውቁበት ሥርዐት ቀብቶ ሥልጣን መስጠቱ አንድም የተደነገገውን ሥርዐት ከመሻር፤ አንድም ሌሎች ጳጳሳትን ቸል ከማለት ጋር የሚያያዝ አይመስለኝም፡፡ ይልቁንም የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቅድስና፣ ታላቅነት ማላቅ እንጂ፡፡ ምክንያቱም የተጋዳሊ ደንቡ፣ የተጋድሎና የበረከት ብሂሉ ይሔው ስለ ኾነ፡፡ ለዚኽም ሳይኾን ይቀራል የጳጳሳቱ ከግብጽ መምጣት የዘገየውና አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከተሾሙ በኋላ የአቡነ ዮሐንስ መምጣት፣ እንደ ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያኗ ጽሑፋዊ መረጃም ኾነ ቃላዊ ተረኮች ጥቆማ አንድም የአጋንንት ምስል እየቀል መኾኑ፤ አንድም ሃይማኖታዊውን የተጋድሎ ብሂል ለማደናቀፍ የተሰማሩ ኃይላት እንደኾኑ ይታመናል፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አስተምህሮ የመተተኞችም ግብር ከዚኽ ውጪ አይታይም፡፡ ይልቁንም በተለያየ ምሥል፣ ቀለም፣ ቅርጽ፣ ወዘተ… ኹለንተናን እየ ለዋወጡና የተለያዩ ተአምራትን እየ ከወኑ የአጋንንትን

[104]ዳን. ፫÷፩-፳፰፡፡

[105]አስ. ፯÷፱-፲፡፡

[106]ዳንኤል፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፵፡፡

[107]አባ ኪዳነ ማርያም ብርሃን፣ ካሴት ቍጥር 3A-B, መጋቢት ፳፻፯ ዐ.ም፡፡

[108]ፍትሐ ነገሥት፣ ፲፱፻፺፯፣ ገጽ ፳፰-፴፯፡፡

ርእዮተ ዐለም የሚያቀነቅኑ እንደ ኾነም ይነገራል፡፡

> አምቦ ሜዳ በሚባለው ቦታ ላይ ኾነው እንደ አውሬ እየ ኾኑ ማስፈራራት ጀመሩ፡፡ የአባታችን ደቀ መዛሙራትም እጅግ ፈሩ፡፡ የእሳትም ፍም በእጃቸው ወደ ዋሻው ይወረውሩ ነበር፡፡ ከዚም አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዋሻቸው ወጥተው በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለው ከአማተቡ በኋላ አንቺ መሬት ተከፍተሽ ዋጫቸው፤ ብለው አዘዟት፡፡ ምድሪቱም እንደታዘዘችው ተከፍታ ዋጠቻቸው፡፡[109]

በተረኩ መተተኞቹ እንደ አውሬ ይኾናሉ፤ የእሳት ፍም ጨብጠው እንደሚወረውሩም ተገልጿል። እዚኽ ላይ መተተኞች በተለያዩ ምትሐቶች ሰዎችን ያሸብራሉ በሚባሉ ምሥሎች ራሳቸውን እንደሚገነቡ ወይም እንደሚገልጡ እንረዳለን፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር በደብረ ዐስቦ ዋሻ ውስጥ ነው ያሉት። መተተኞቹ ደግሞ የተለያዩ ገቢራትን የሚከውኑት፣ ፍም የሚወረውሩት አምቦ ሜዳ[110] ላይ ኾነው ነው። በመልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ደረጃ በመሐላቸው (በደብረ ዐስቦና በአምቦ ሜዳ) መጠነኛ መራራቅ አለ። በኋላ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ትእዛዝ መሠረት መሬት (ምድር) መተተኞቹን ተከፍታ ትውጣለች፡፡ በቤተ እምነቱ ከተደነገገው ሥርዐት ለወጣ፣ በተቃርኖ ለቆመ፣ በጠላትነት ለተነሣ፣ ወዘተ… ብድራቱን ጠቋሚ ይመስላል።

የቆሬ፣ የዳታንና አቤሮን ኹነት ያነሣሁትን ሐሳብ ያጸናል። ቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን በሙሴና በአሮን ላይ ተነሡባቸው፤ አጉረመረሙባቸውም። ሕዝቡንም ጭምር አስከተሉ። በመጨረሻም ሙሴ ለእግዚአብሔር አመለከተ። ኹሉን ከነወዳጆቻቸው ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው፡፡[111] በተአምረ ማርያም ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኘው ሐሳብም እንዲኹ። "… ዳታንንና አቤሮንን ምድር ተከፍታ እንደ ዋጠቻቸው፣ አንቺንም እንዲኹ እግዚአብሔር ያስጥምሽ" ስትል እመቤታችን ረገመቻት። … ይኽ የመርገም ቃል ተነግሮ ሳያልቅ ያቺን ሴት ምድር ተከፍታ ዋጠቻት፡፡[112] በሦስቱም ተረኮች አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ሙሴ እና ድንግል ማርያም የተነሡባቸውን ምድር ተከፍታ እንድትውጣቸው የሚያመለክቱት ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር ነው። ለእያንዳንዳቸው የተደረገው ምላሽም ይገጥማል።

እዚኽ ላይ፣ በሦስቱ ተረኮች የሚትን ሰንሰለታዊ ቅብብሎሽ እንረዳለን፡፡ ሚት የማይቋረጥ፣ የማይገደብ፣ በዘመናት እንደ ጅረት የሚፈስ፣ ይልቁንም በሀልዎቱ የሚጸና መኾኑን ከተረኮቹ እንገነዘባለን፡፡

[109]አባ ሠረገላ ገብረ ሕይወት፣ ካሴት ቁጥር 5A, መጋቢት ፳፻፮ ዐ.ም፡፡

[110]አምቦ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ቅጥር ውስጥ የምትገኝ ሥፍራ ናት፡፡ ሥፍራዋ ሜዳማ ስትኾን ምንጭም ይፈልቅባታል፡፡ ወዲኽ በሚፍልቀው ውኃ በርካታ ድውያን እንደሚፈወሱ፤ ወዲያም አቡነ ተክለ ሃይማኖት መተተኞች አውሬ መስለው በቦታው ላይ ኾነው ሲያንሩ ተከፍታ እንድትውጣቸው ያዘዟትም እንደ ኾነች ይነገራል።

[111]ዘኁ. ፲፮÷፩-፴፫፡፡

[112]ተስፋ፣ ፲፱፻፹፰፣ ገጽ ፻፴-፻፴፩፡፡

በሙሴ ዘመን እነ ቆሬ (ብሉይ ኪዳን)፣ በድንግል ማርያም ደግሞ ትእማር (የዘመነ ሐዲስ ጅማሮ /ከ፩-፫ ዐ.ም/)፣ በመጨረሻም ከ፲፪፻፶ ዐመት ገደማ በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መሰል ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡ ስለዚኽ ይኽ ሚታዊ ብሂል በየዘመናቱ መሠረተ ሐሳቡን ሳይጥስ፣ መልኩን ግን እንደየ ዘመኑ መንፈስና ንጽረተ ዐለማዊ እሳቤዎች እየ ለዋወጠ ህልው ኾኖ ይዘልቃል ማለት ይቻላል፡፡

## ፫. መደምደሚያ

ይኽ ጥናት በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከቃል ኪዳን፣ ከፈውስ፣ ከስያሜ እና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች ጥናት በሚል የተዘጋጀ ነው፡፡ መረጃዎች፣ ወዲኽ በቃለ መጠይቅና በምልከታ ተሰንደዋል፤ ወዲያ ደግሞ የተሠነዱት ተረኮች በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ እና በተረክ ንድፈ ሐሳብ መታገጊያነት ተፈክረውና ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ተረኮቹን በበይነ-ጽሑፋዊ (inter-textual) ብልሃት ከሚጠሯቸው ድርሳናት፣ መጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይና ሐዲስ) እና ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮች ጋር እያዋገኑ በማናበብ ፍቺ ለማበጀት ተሞክሯል፡፡

በዚኽም፣ ተረኮቹ አንድም  የገዳሙን ቅጥር የማበጀት፣ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን የተጋድሎ ብሂል የመትከል ሚና እንዳላቸው ታውቋል፤ አንድም የታሪካዊ ኹነት አስረጂ፣ የገዳሙንና የገዳማውያንን ርእዮተ ዐለም የመዘከር ተግባራቸውም በጥናቱ ተመልክቷል፤ አንድም የሚትን ዘለዐለማዊነት በአንድ በኩል የሚያጸኑ፣ በሌላ መልኩ ደግሞ የሚያዘልቁ እንደ ኾኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ተረኮቹ የሚጠሯቸው ሌሎች ሚታዊ ተረኮች (መንፈሳዊ /መጽሐፍ ቅዱሳዊ/ ተረኮች) አሉ፡፡ እነዚኽ ተረኮች በአቀራረብ ሒደት የተለየ መልክ ቢኖራቸውም መሠረተ ሐሳባቸው ግን አይፋለስም፡ ፡ ስለኾነም ከጥንት እስከ አኹን (ከብሉይ እስከ ሐዲስ ልንለው እንችላለን) በተለያዩ ሽለቆዎች እየ ዘመቱ ኋላ ከአንድ ወንዝ፣ ከአንድ ባሕር ይገጥማሉ፤ ትባሬያቸውም ይጸናል፡፡ በመጨረሻም ተረኮቹ ተራኪዎቹ (ገዳማውያኑ) መትከል ለሻቱት ርእዮተ ዐለም በጅተዋል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

 © ጥናትና ምርምር ማእከል ፣ ማኅበረ ቅዱሳን